ምዕራፍ ዘጠኝ

በደርቡሾች የጠፉ፣ የተቃጠሉና የተመዘበሩ አብያተ ክርስቲያናት

23. ማኅበረ ሥላሴ ገዳም

ማኅበረ ሥላሴ ገዳም መገኛው በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት መተማ ወረዳ ደረቅ ዓባይ ከተባለች የገጠር ከተማ ከዐራት ሠዓት የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው። ማኅበረ ሥላሴ የተመሠረተው በ4ኛው[117] መ.ክ.ዘ. ነው።

አብያተ ክርስቲያናትን በማነጹና ክርስትናን በማስፋፋቱ ረገድ ቀዳሚ የነበሩት መንትዮቹ ነገሥታት አብርሃ ወ አጽብሐ ከወቅቱ ጳጳስ ከአቡነ ሰላማ ጋር በመሆን እየተዘዋወሩ ወንጌልን በሚያስፋፉበት ጊዜ ቀድሞ አይክል ትባል በነበረችው የዛሬዋ ጭልጋ ከተማ ልዩ ስሟ ጉባኤ በተባለች ቦታ ይደርሱና ጸሎት ማድረግ ይጀምራሉ። ጸሎታቸውን ሲያጠናቅቁ ዛሬ ማኅበረ ሥላሴ ካለበት ቦታ ላይ ሦስት የብርሃን አእማድ ተተክሎ ያያሉ። ነገሥታቱ ምንነቱን ለማወቅ ጳጳሱን ይጠይቋቸዋል። ጳጳሱም ሦስቱ የብርሃን አእማድ የሥላሴ ምሳሌ መሆኑን ይነግሯቸዋል። ቦታውም ረድኤተ እግዚአብሔር የረበበበት ቦታ መሆኑን ይገልጹላቸዋል። ነገሥታቱ የጳጳሱን ገለጻ ሰምተው ሲያበቁ ወደ ቦታው ያመራሉ። ቤተ ክርስቲያንም ይሠራሉ። ምቋመ ሥላሴ ብለው ስም ያወጡለታል።

አባ ዓምደ ሥላሴ

❖ አባ ዓምደ ሥላሴ የሸዋ ሰው ናቸው። ጸሐፊው ያልተጠቀሰ ስለዋታም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ታሪክ የሚያትት ባለስድስት ገጽ የኮምፒውተር ጽሑፍ እኚህ

[117] - አንዳንድ ድርሳናት የተመሠረተው በዐጤ ሱስንዮስ ዘመን ነው ይላሉ። እንደነዚህ ድርሳናት ከሆነ መሥራቹ አባ ዓምደ ሥላሴ የተባሉ የበቁ መነኩሴ ናቸው። ነገር ግን ተረኩ ከእውነታው ጋር ይጣረሳል። ባሕታዊው ዓምደሥላሴ ገዳሙን በዚህ ዘመን መጥተው አቀኑት እንጂ አልመሠረቱትም።

አባት ወደዚህ ቦታ የመጡት በ16ኛው መ.ክ.ዘ. ማብቂያ ላይ ሊሆን እንደሚችል የሚያስገምት ታሪክ በመጀመሪያ ገጹ ላይ አስፍሯል።

ይህንኑ ታሪክ የሚያጠናክር ሀተታ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች በገጽ 147 ላይ አሳፍሮ እንደሚያስነበበን ከሆነ እኚህ አባት ገዳሙን የመሠረቱት ከዐጤ ሱስንዮስ መንገሥ ዐሥር ዓመታት ቀደም ብሎ በ1590 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ነው። ነገር ግን ዐጤ ሱስንዮስ የነገሡት በ1597 ዓ.ም ነው። እውነቱ ይህ ከሆነ አባ ዓምደ ሥላሴ ገዳሙን የመሠረቱት አንድም ዐጤው ከመንገሣቸው ሰባት ዓመት በፊት ሁለትም ቀዳሚው ዐሥር ዓመት ከሆነ 1587 ዓ.ም ነው።

ልዑል ፋሲል አባታቸው ዐጤ ሱስንዮስ ታመው አንደበታቸው በተዘጋ ጊዜ ተጨንቀው በየቦታው ወዳሉት ገዳማትና አድባራት "በጸሎታችሁ እርዱኝ፣ አባቴን አድኑልኝ ያላችሁትን ሁሉ አደርጋለሁ" እያሉ መብዓ እያስያዙ መልእክተኞችን በላኩ ጊዜ መልዕክቱ ማኅበረ ሥላሴ ደረሰ። ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ 138 እና 139 ላይ እንደሚተርኩት ከሆነ አባ ዓምደ ሥላሴ "ለገዳሙ መተዳደሪያ የሚሆን 44 ጉልት ከሰጠኸኝ እኔ አባትህን አድንልሃለሁ" የሚል መልዕክት ለልዑሉ ይልካሉ። ልዑሉም እሺ ብሎ እንዲመጡ መልዕክት ልኮባቸዋል።

አባ ዓምደ ሥላሴ ተነስተው መነኰሳቱን አስከትለው ደንቀዝ ይገባሉ። ሦስት ሰባኤ ሌሊትና ቀን በጸሎት ቆመው ፈጣሪያቸውን ለምነው ሱስንዮስን አጥምቀው አቆረባቸው። ታማሚውም ንጉሡ በዚህ ጊዜ አንደበታቸው ተከፈተ። መነኩሴውም "ካቶሊክ ትርከስ አርቶዶክስ ትመለስ" ብለህ አዋጅ አስነግር አሏቸው። ዐጤ ሱስንዮስም እንደተባሉት አደረጉ።

አዋጁ ከታወጀ በኋላ በዳር በገደሉ ያለው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አማኝ ወደየቤቱ መመለስ ጀመረ። አንዳንድ ድርሳናት አባ ዓምደ ሥላሴ በተፈጠረው የሃይማኖት ትርምስ ወደ ስናር በረሃ ተሰደው ይኖሩ ነበር። ወደ ገዳማቸው የተመለሱት ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ የሚለው አዋጅ ከታወጀ በኋላ ነው። አተራረክ ተዓማኒነት የለውም።

ምዕራፍ ዘጠኝ

በደርቡሾች የጠፉ፣ የተቃጠሉና የተመዘበሩ አብያተ ክርስቲያናት

23. ማኅበረ ሥላሴ ገዳም

ማኅበረ ሥላሴ ገዳም መገኛው በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት መተማ ወረዳ ደረቅ ዓባይ ከተባለች የገጠር ከተማ ከዐራት ሠዓት የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው። ማኅበረ ሥላሴ የተመሠረተው በ4ኛው[117] መ.ክ.ዘ. ነው።

አብያተ ክርስቲያናትን በማነጹና ክርስትናን በማስፋፋቱ ረገድ ቀዳሚ የነበሩት መንትዮቹ ነገሥታት አብርሃ ወ አጽብሐ ከወቅቱ ጳጳስ ከአቡነ ሰላማ ጋር በመሆን እየተዘዋወሩ ወንጌልን በሚያስፋፉበት ጊዜ ቀድሞ አይከል ትባል በነበረችው የዛሬዋ ጭልጋ ከተማ ልዩ ስሟ ጉባኤ በተባለች ቦታ ይደርሱና ጸሎት ማድረግ ይጀምራሉ። ጸሎታቸውን ሲያጠናቅቁ ዛሬ ማኅበረ ሥላሴ ካለበት ቦታ ላይ ሦስት የብርሃን አእማድ ተተክሎ ያያሉ። ነገሥታቱ ምንነቱን ለማወቅ ጳጳሱን ይጠይቋቸዋል። ጳጳሱም ሦስቱ የብርሃን አእማድ የሥላሴ ምሳሌ መሆኑን ይነግሯቸዋል። ቦታውም ረድኤተ እግዚአብሔር የረበበበት ቦታ መሆኑን ይገልጹላቸዋል። ነገሥታቱ የጳጳሱን ገለጻ ሰምተው ሲያበቁ ወደ ቦታው ያመራሉ። ቤተ ክርስቲያንም ይሠራሉ። ምቋመ ሥላሴ ብለው ስም ያወጡለታል።

አባ ዓምደ ሥላሴ

- አባ ዓምደ ሥላሴ የሸዋ ሰው ናቸው። ጸሐፊው ያልተጠቀሰ ስለዋታም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ታሪክ የሚያትት ባለስድስት ገጽ የኮምፒውተር ጽሑፍ እኒህ

[117] - አንዳንድ ድርሳናት የተመሠረተው በዐጤ ሱስንዮስ ዘመን ነው ይላሉ። እንደነዚህ ድርሳናት ከሆነ መሥራቹ አባ ዓምደ ሥላሴ የተባሉ የበቁ መነኩሴ ናቸው። ነገር ግን ተረኩ ከእውነታው ጋር ይጣረሳል። ባሕታዊው ዓምደሥላሴ ገዳሙን በዚህ ዘመን መጥተው አቀኑት እንጂ አልመሠረቱትም።

አባት ወደዚህ ቦታ የመጡት በ16ኛው መ.ክ.ዘ. ማብቂያ ላይ ሊሆን እንደሚችል የሚያስገምት ታሪክ በመጀመሪያ ገጹ ላይ አስፍሯል።

ይህንኑ ታሪክ የሚያጠናክር ሀተታ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች በገጽ 147 ላይ አሳፍሮ እንደሚያስነብበን ከሆነ እኚህ አባት ገዳሙን የመሠረቱት ከዐጤ ሱስንዮስ መንገሥ ዐሥር ዓመታት ቀደም ብሎ በ1590 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ነው። ነገር ግን ዐጤ ሱስንዮስ የነገሡት በ1597 ዓ.ም ነው። እውነቱ ይህ ከሆነ አባ ዓምደ ሥላሴ ገዳሙን የመሠረቱት አንድም ዐጤው ከመንገሣቸው ሰባት ዓመት በፊት ሁለትም ቀዳሚው ዐሥር ዓመት ከሆነ 1587 ዓ.ም ነው።

ልዑል ፋሲል አባታቸው ዐጤ ሱስንዮስ ታመው አንደበታቸው በተዘጋ ጊዜ ተጨንቀው በየቦታው ወዳሉት ገዳማትና አድባራት "በጸሎታችሁ እርዱኝ፣ አባቴን አድኑልኝ ያላችሁትን ሁሉ አደርጋለሁ" እያሉ መብዓ እያስያዙ መልእክተኞችን በላኩ ጊዜ መልዕክቱ ማኅበረ ሥላሴ ደረሰ። ተክለ ጻድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ 138 እና 139 ላይ እንደሚተርኩት ከሆነ አባ ዓምደ ሥላሴ "ለገዳሙ መተዳደሪያ የሚሆን 44 ጉልት ከሰጠኸኝ እኔ አባትህን አድንልሃለሁ" የሚል መልዕክት ለልዑሉ ይልካሉ። ልዑሉም እሺ ብሎ እንዲመጡ መልዕክት ልኮባቸዋል።

አባ ዓምደ ሥላሴ ተነስተው መነኰሳቱን አስከትለው ደንቀዝ ይገባሉ። ሦስት ሰባኤ ሌሊትና ቀን በጸሎት ቆመው ፈጣሪያቸውን ለምነው ሱስንዮስን አጥምቀው አቆረቧቸው። ታማሚውም ንጉሡ በዚህ ጊዜ አንደበታቸው ተከፈተ። መነኩሴውም "ካቶሊክ ትርከስ አርቶዶክስ ትመለስ" ብለህ አዋጅ አስነግር አሏቸው። ዐጤ ሱስንዮስም እንደተባሉት አደረጉ።

አዋጁ ከታወጀ በኋላ በዱር በገደሉ ያለው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አማኝ ወደየቤቱ መመለስ ጀመረ። አንዳንድ ድርሳናት አባ ዓምደ ሥላሴ በተፈጠረው የሃይማኖት ትርምስ ወደ ስናር በረሃ ተሰደው ይኖሩ ነበር። ወደ ገዳማቸው የተመለሱት ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ የሚለው አዋጅ ከታወጀ በኋላ ነው። አተራረክ ተዓማኒነት የለውም።

ባሕታዊው ለሃይማኖት መመለስና ሱስንዮስን ከዱዳነት ለማዳን ከፍተኛ መንፈሳዊ ተጋድልኦ መፈጸማቸው በበርካታ ድርሳናት ላይ ተተርኪል። ልዑል ፋሲል ለአባ ዓምደ ሥላሴ ቀድመው በገቡት ቃል መሠረት ከጣቁሳ 44 ጉልት ሰጧቸው። ባሕታዊው ወደ ገዳማቸው ተመልሰው በመንፈሳዊ ተግባራቸው መትጋታቸውን ቀጠሉ። በመጨረሻም በተወለዱ በአንድ መቶ ዐራት ዓመታቸው የካቲት 27 ቀን ከዚህ ዓለም በሥጋ ሞት ተለዩ። ከእሳቸው ሕልፈት በኋላ የአስተዳደር ኃላፊነቱን የተረከቡት ከዋታም አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ የአስተዳደር ሥራ ጋር ደርበውና አቀናጅተው የሠሩት አባ ክፍለ ማርያም ናቸው።



ፎቶ. በማኅበረ ሥላሴ ገዳም የተማሩት ዐጤ ቴዎድሮስ

አባ ዓምደ ሥላሴ እና አባ ክፍለ ማርያም በታላቅ መንፈሳዊ ጽናት በተጋደሉበት በዚህ ጥንታዊ ገዳም ውስጥ ታላቁ መሪ ዳግማዊ ዐጤ ቴዎድሮስ የአብነት ትምህርት ተምረውበታል። እሳቸው በሚማሩበት ጊዜ ወረርሽኝ ተነስቶ ብዙዎችን ለሕልፈተ ሕይወት ሲዳርግ እርሳቸው ግን ተርፈዋል።

ደርቡሾች የደምቢያውን ሹም ዳኅና ፈንታን ወግተው ድል ከአደረጉ በኋላ ይህን ገዳም አቃጥለውታል። <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u> ገጽ 148 ላይ የማኅበረ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለው ጥር 27/ 1877 ዓ.ም እንደሆነ ይገልፃል። ደርቡሾች ማኅበረ ሥላሴን ካቃጠሉ

በኋላ የጎጃሙ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በዐጤው ትዕዛዝ መጥተው ሲገጥሟቸው ድል አድርገዋቸው ወደ ጎንደር ከተማ ገስግሰዋል። ታሪኩ እንዲህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የተቃጠለው 1877 ዓ.ም አይሆንም። ምክንያቱም ደርቡሾች ጎንደር ለመጀመሪያ ጊዜ የገቡት በ1880 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ነበር።

ዓመተ ምሕረቱ መቼም ይሁን መቼ ገዳሙ በደርቡሾች የጥፋት ሰለባ መሆኑ እርግጥ ነው። ቅርሱ ተዘርፏል። መነኮሳቱ ታርደዋል። ቤተ ክርስቲያኑ ከዚህ ጥፋት በኋላ ድጋሚ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ምኒልክ ተሠርቷል። ንግሥቲቷ ሁለት የውኃ ማጠራቀሚያ ገንዳ ለገዳማዊያኑ አሠርተዋል። ማኅበረ ሥላሴ በጥፋት እጆች ጉዳት የደረሰበት በደርቡሾች ብቻ አይደለም። ጣሊያኖችም ሚያዚያ 13 ቀን ቤተ ክርስቲያኑን በቦንብ አጋይተውታል። መነኮሳቱንም ኢ-ሰብዓዊነት በተመላበት ጭካኔ ገድለዋቸዋል። መነኮሳቱ የተገደሉት ቤተ ክርስቲያኑ ከተቃጠለ ከሁለት ቀናት በኋላ ሚያዚያ 15 ቀን 1928 ዓ.ም ነው። ፋሺስቶች በገዳሙና በገዳማዊያኑ ላይ የሚያደርጉት ግድያ በዚህ አላበቃም። ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቦታው ዘምተው፦ሐምሌ 7 ቀን 1929 ዓ.ም መነኮሳቱን ገድለዋል። በዕለቱ የተገደሉት መነኮሳት ቁጥር 25 ነበር።

የገዳሙ መናንያን ምግብ ከጤፍና ከማሽላና ከዳጉሳ ዱቄት ድብልቅ የሚዘጋጅ አነባበሮ ነው። ገዳሙ ውስጥ ከውጪ የሚመጣ የበሰለ ምግብ አይገባም። የጦር መሳሪያ ይዞ መግባት በፍፁም የተከለከለ ነው። ጫማ አድርጎ መግባትም እንዲሁ። በአሁኑ ጊዜ የገዳሙ የአስተዳደር ሥራ የሚመራው በስድስት አባቶች ነው። እነዚህ ስድስቱ አበምኔት፣ ዕጓለ መጋቢ፣ ሊቀ ረድኤ፣ ሰጠኝ ዕቃ ቤት፣ ሊቀ አበውና መጋቢ ናቸው።

ምንጭ

-ስሙ ያልተጠቀሰ ጸሐፊ። የዋታዎ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም ታሪክ። /የኮምፒውተር ጽሑፍ/
-የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት። ቅጽ 2 ገጽ 184
-የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት። ቅጽ 9 ገጽ 91
-አባ ጎርጎርዮስ። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። ገጽ 53
- ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት። ዝኒ ከማሁ። ገጽ 44— 450

- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ። ገጽ 65-72
- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ዝኒ ከማሁ። ክገፅ 147-148
- ባሕረ ሃሳብ ገጽ 272 — 273
-ጆሴፍ ፍራንሲስ። /ተርጓሚ ነብይ መኮንን/ ዓለማየሁ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያዊው ልዑል። አዲስ አበባ፣ 1999። ገጽ 8

24.ጎንደር ልደታ ለማርያም

በጎንደር ካሉት 44 አብያተ ክርስቲያናት መሐከል የመካነ ስብሐት ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን አንዷ ስትሆን የተተከለችው በንጉሠ ነገሥት ዐጤ ዮስጦስ ዘመነ መንግሥት በ1703 ዓ.ም ነው። የተከሏትም እኅሁ ንጉሥ /ዐጤ ዮስጦስ/ ናቸው። ንጉሡ ቦታውን ከባለእርስቶች ላይ ገዝተው ነው ቤተ ክርስቲያኗን ለመትከል የበቁት። ዕላቷን ያመጧትም ከትግራይ እንደሆነ ይነገራል።

የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች በተሰኘው በዲያቆን ዳንኤል ክብረት መጽሐፍ ገጽ 21 ላይ እንደተገለጸው ከሆነ ንጉሡ ተቦታን ከተከሉ በኋላ በግብዝና የሚያስቴይድሩ 50 መኳንንት፣ 50 ወይዛዝርት፣ 50 ደባትር በአጠቃላይ መቶ ሀምሳ አገልጋዮችን መድበውላታል። ለመተዳደሪያ የሚሆን መሬትም በደምቢያ ወረዳ የሰባት ጭቃ ሹም ሪም መሬት ሰጥተዋል።

ሪም ማለት ለገጠር ቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ የእርሻ መሬት ነው። ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተሰኘ መጽሐፋቸው የቤተ ክርስቲያኗ ሥሪት የገዳም፣ የደብርና የገጠር ሥሪት ነው ብለው በሦስት ያስቀምጡታል። ከሦስቱ ውስጥ የገጠር ቤተ ክርስቲያን ርስት ጉልት የለውም። ስለሌለውም ቤተ ክርስቲያን የሚሠራው ለሃይማኖቱ ቀናኢ የሆነው ገበሬው ነው። እንደ ብፅዕነታቸው ገለጻ ከሆነ ገበሬው ለሠራው ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የሚሆን የተወሰነ የእርሻ መሬት ይመድባል። ይህም ሪም ይባላል።
/ለተጨማሪ መረጃ ዝኒ ከማሁ ገጽ 160/

ዛሬ በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት ስር ያለችው ይህቺ ቤተ ክርስቲያን በጎንደር ከተማ መግቢያ ላይ ትገኛለች። ተካይዋ ንጉሥ ዘመዳቸው በሆነውና ዳዊት በተባለው ዘፋኝ ከተገደሉ በኋላ በዚህችው ቤተ ክርስቲያን ምሥራቃዊ አቅጣጫ ከሕንጻው ጋር በተያያዘ መቃብር ቤት ውስጥ አስከሬናቸው በክብር አርፏል። የዐጤ ዮስጦስ ዘመነ መንግሥት አጭር ስለነበረ ቤተ ክርስቲያኗን ሳይጨርሷት በመሞታቸው ምክንያት ዐጤ በካፋ ጨርሰዋታል። በጎንደር ልደታ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መምህር ኤስድሮስ የሚባሉት ታላቅ ሊቅ ያስተምሩ ነበር።

መምህር ኤስድሮስ

❖ እኚህ ሊቅ ዐራት ዓይና የተባሉ የብሉያትና የሐዲሳት መምህር፤ የዐራቱ ጉባኤያት ሊቅ የነበሩ ናቸው። ትውልዳቸው ትግራይ ተንቤን ሲሆን በተወለዱ በሦላሳኛ ቀናቸው የዓይን ብርሃናቸውን በፈንጣጣ በሽታ አጥተዋል። መመህር ኤስድሮስ ዩዐሥራ አንድ ዓመት ታዳጊ ሳሉ አባ ሐደራ ከተባለ ገዳም ገብተው መማር ጀመሩ። በገዳሙ ከፊደል ቆጠራ እስከ ዳዊት ደገማና ጸዋትወ ዜማ ያለውን ትምህርት ተምረዋል። ከዚህ በተረፈ ያለውን ትምህርት <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u> በሚለው መጽሐፍ ላይ እንደሚከተለው ሰፍሯል።

"የትርጓሜ መጽሐፍትን ትምህርት የተማሩበት ቦታ ምናልባት በጎንደር ሊሆን እንደሚችል የመጽሐፉ አዘጋጅ ይገምታል። የቅኔ ትምህርታቸውን በተመለከተ ግን በአክሱም ጽዮን ማርያም መማራቸውን አለቃ ዓምደ ጽዮን ይተርካሉ።

"በጎንደር ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ከቆዩ በኋላ ያልተማርነው ነገር አለ በማለት ወደ ጣና ገዳማት በመግባት በተለይም በዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ገብተው ሦስት መቶ መጽሐፍትን መረመሩ። እግረ መንገዳቸውንም በጥንታዊያን ሊቃውንት የተጻፉ ከቀድሞው ስልት አጠር ያለ ነገር ግን ብዙ ምሥጢር ያለበት ትርጓሜ ማግኘታቸው ይነገራል።"

/ዝኒ ከማሁ ገጽ 23 /

መምህር ኤስድሮስ በታላላቅ ገዳማት እየተዘዋወሩ ከ300 በላይ መጽሐፍትን መርምረዋል። በምርምራቸውም የቀደመውን ትርጓሜ ስልት እንደገና አቃንተውታል። በዚህም ረገድ አዲስ ምዕራፍ ከፍተዋል። ከጣና ገዳማት ከተመለሱ

በኋላ አዳዲስ ትርጓሜን ጨምረው ረጅም የነበረውን የትርጓሜ ስልት አሳጥረው ለተማሪ በሚያመች መልኩ አቀናብረውታል። በመቀጠልም የቀድሞ ተማሪዎቻቸውን "ኑ የቀረን ነገር አለና እንመርምር" ብለው ጥሪ አቅርበውላቸዋል። ብዙዎቹ ጥሪያቸውን ሰምተው መጡ። ጥቂቶቹ ግን ቀሩ።[118] በእነዚህ ተማሪዎች መምጣትና መቅረት ብሎም በቀድሞውና በአዲሱ የመምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ መሠረት የመጽሐፍት ትርጓሜ ለሁለት ተመደበ። በአመዳደቡም መሠረት አዲሱና የመምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ "የታች ቤት ትርጓሜ" ተባለ። መምህር ኤስድሮስ ሊጠሯቸው አንመጣም ብለው የቀሩትና ያስቀጠሉት የቀድሞው ትርጓሜ ደቀ መዛሙርት ደግሞ "የላይ ቤት ትርጓሜ" ተባለ።



ፎቶ. መምህር ኤስድሮስ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ሲያስተምሩ


የእሳቸውን ፈለግ ብዙዎቹ ተከትለዋል። ከብዙዎቹና ከታወቁት ሊቃውንት መሐከል መማር አንደ አካልዬ የተባለላቸው መምህር አካለ ወልድ፤ የግምጃ ቤት ማርያም መምህር የሆኑት መምህር ወልደ አብ፤ የዜና ማርቆስ መምህር ወልደ ማኅሌል ለአብነት ያህል ይጠቀሳሉ።

---

118 - የቀድሞዎቹ ተማሪዎቻቸው ጥሪው ሲደርሳቸው «እኛ ቀድሞ የተማርነውን እናስተምራለን » ብለው ቀርተዋል። ያሻሻሉትን ትርጓሜ አዲስ ለተቀበሏቸው ተማሪዎች አስተማሩ ይላሉ መልአከ ምክር ከፍያለው መራሒ።
/ዝክረ ሊቃውንት። አዲስ አበባ፤ 2003/

ወደ ቀድሞ ነገራችን እንመለስ፤ ወደ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን። ደርቡሾች ጎንደርን በወረሩበት ዘመን ቤተ ክርስቲያኗን አፈራርሰው በእሳት አቃጥለዋታል። ይህ የሆነው በ1880 ዓ.ም ነው። ዘመኑ ደርቡሾች ለመጀመሪያ ዘመን ወደ ጎንደር ገብተው ለጥፋት የተሰማሩበት ዘመን ነው።

ቤተ ክርስቲያኗ በደርቡሾች ከተቃጠለች በኋላ የሸዋው ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ገንዘብ ልከው አሠርተዋታል የሚል አተራረክ አስፍረው የሚያስነብቡን መጽሐፍት[119] አሉ። ይህ ታሪክ ከእውነታው ጋር ይጣረሳል።



ፎቶ. በደርቡሽ ጉዳት የደረሰባት ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያኒቷ የተቃጠለችው በደርቡሾች ነው፤ ዘመኑም 1880 ዓ.ም። ታሪኩ ይህ ከሆነ ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ድጋሚ ሊያሠሯት አይችሉም። ምክንያቱም ንጉሡ በዚህ ዘመን በሕይወት አልነበሩም። የሞቱት በጥቅምት 12 ቀን 1840 ዓ.ም ነው። በዚህ የዘመን ስሌት መሠረት በንጉሡ ሞትና በቤተ ክርስቲያኗ መቃጠል መሐከል የዐርባ ዓመታት ልዩነት አሉ።

[119] የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች ገጽ 22

የጎንደር ልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ባደረገው ትብብር ከ1938-1939 ዓ.ም ተሠርቷል። ቀድሞ ቦታው "መካነ ስብሐት" የሚል መጠሪያ የነበረው ሲሆን አለቃውም "መልአከ ስብሐት" የሚሰኝ ስመ ማዕረግ ነበራቸው። ይህ አጠራር እስከዛሬ ድረስ ዘልቋል። ዐጤ በካፋ የቤተ ክርስቲያኗን ቅፅር፤ በአጠቧም ለራሳቸው የምትሆን እልፍኝ አሠርተው ነበር። በወቅቱ አለቃ የነበሩት ሰው መልአከ ስብሐት ፀሐየ ልዳ ይባሉ ነበር።

የጎንደር ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን የተተከለችው በ1717 ዓ.ም በዐጤ ዮስጦስ ዘመነ መንግሥት እንደሆነ የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች ይተርካል። እዚህም ጋር የታሪክ መጣረስ ይታያል። ይኸውም 1717 ዓ.ም የዐጤ ዮስጦስ ዘመን መሆኑ ነው። ነገር ግን የዐጤ ዮስጦስ ዘመነ መንግሥት ከ1703 ዓ.ም እስከ 1708 ዓ.ም ነበር። ዘመነ ግዛታቸውም ዐራት ዓመት ከዐራት ወር ያህል ነው። አንዳንድ ድርሳናት የንጉሡን የግዛት ዘመን 5 ዓመት ያደርጉታል።

ዐጤ ዮስጦስ

- ዮስጦስ የነገሡት ከዐጤ ቴዎፍሎስ ቀጥሎ ነው። እሳቸው ከዐጤ ዮሐንስ አንደኛ ልጅ ከአድያም ሰገድ ዐጤ ኢያሱ እና ከልጃቸው ከተክለ ሃይማኖት ቀጥሎ ዙፋኑን በያዙት በወንድማቸው በዐጤ ቴዎፍሎስ ዘመን ቤጅሮንድ፤ ኋላም ራስ ተብለው በታማኝ ባለሟልነት አገልግለዋል። ዐጤ ቴዎፍሎስ ሲሞቱ ግን ወደ ዙፋን ሲመጡ ዘውድ ለመድፋት ከባድ ፈተና ገጥሟቸው ነበር። የፈተናው መነሻ ከነገሥታት አይወለዱም የሚል ነበር። በዚህም የተነሣ ጎንደሬዎች ለሦስት ተከፍለዋል። ግማሻቸው በዐጤ ዮስጦስ በኩል ሲሆኑ የሳቸውን መንገሥ የተቃወሙት ደግሞ በሁለት ጎራ ተከፍለዋል፤ ግማሾቹ *በካፋ ይንገሥ ሌላው ደግሞ ዳዊት ይንገሥ* ይባባሉ በሚል ክርክር።

  የኋላ ኋላ ግን ፈተናውን አልፈውት ዐጤ ዮስጦስ መንበረ መንግሥቱን ጨበጡ። እነዚያን ሲቃወሟቸው ነበሩትን ሰዎች እያሳደዱ ቀጧቸው። ከቅጣት የተረፉትንም ከሥልጣናቸው ሽረው ሁነኛ በሚባለው የሥልጣን እርከን ላይ የራሳቸውን ሰዎች ሾሙ። ሕዝቡም በአሜንታ ተቀበላቸው። ሲነግሡ ስመ መንግሥታቸው ፀሐይ ሰገድ ተሰኝቷል። በመጨረሻም ዐራት ዓመት ከዐራት ወራት በሥልጣን ቆይተው በ1708

ዓ.ም የአባ አንጦንስን ቤተ ክርስቲያን ለመሳለምና ሥራቸውንም ለማየት በሔዱበት ጊዜ ታመመና ወደ ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ። በዚህ ሕመማቸው ላይ እያሉ ሣልሳዊ ዐጤ ዳዊት አድባር ሰገድ ተብለው ዙፋኑን ያዙ። ዮስጦስም ዐጤ ዳዊት በነገሡ በዘጠንኛው ቀን ሞቱ። ራሳቸው ባሠሯትና አሁን ታሪካዊ በሚዘከርላት በልደታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቀበሩ።



ፎቶ. ዐጤ ዮስጦስ የልደታ ማርያምን ታቦት ሲያድቡ

ምንጭ

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ። ገጽ 160
- ታዬ ገብረ ማርያም። /አለቃ/ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ አዲስ አበባ፣1948። ንግድ ማተሚያ ቤት።
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ። ከገጽ 219-222፣ 249።
- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ገጽ 21፣22፣23፣24
- ጎሩይ ወልደ ሥላሴ። /ብላቴን ጌታ/ ዋዜማ። አዲስ አበባ፣2001። ኮምፒዮግራፊ አታሚዎች። ገጽ 65
- መንግሥተ አብ አበጋዝ። ስምዐ ጽድቅ። ቅጽ 18 ቁ. 215፣ ገጽ 1 አዲስ አበባ፣ ታኅሣሥ 2003። ማኅበረ ቅዱሳን።
- ክፍያለው መራሒ። ዝክረ ሊቃውንት።አዲስ አበባ፣ 2003። ንግድ ማተሚያ ድርጅት። ገጽ 21፣ 22፣ 79

- ዜና መዋዕል ዘበጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ ነሐሴ 1978 ዓ.ም ገጽ 22- 23

25. ጎንደር ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን

ጎንደር ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት በጎንደር ከተማ ይገኝ የነበረ ቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያኑን የተከሉት ኃያል ሰገድ በሚል ስመ መንግሥት ዘውድ የደፉት ዐጤ ተክለ ሃይማኖት ናቸው። ንጉሡ መንበረ ዙፋኑን የያዙት አንድ ዓመት ብቻ ከገዙት ዐጤ ዮሐንስ ሁለተኛ /አባታቸው/ ከሞቱ በኋላ ነው። ንጉሡ በ1762 ዓ.ም ሲነግሡ ዕድሜያቸው ገና 15 ዓመት ነበር።

መናኔ መንግሥት ዐጤ ተክለ ሃይማኖትን ያነገሧቸው ራስ ሚካኤል ናቸው። ሚካኤል 1763 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር የዳሞትንና የአገውን ሕዝብ ይዘው ለመዋጋት ፋጊት ላይ የተሰለፈውን ፋሲልን ለመፋለም ዘመቱ። በዚሁ ቦታም ጦርነት ሆነ። በጦርነቱ ዐሥር ሺህ ሰው /ከሁለቱም ወገን/ እንዳለቀ ታሪክ ይናገራል። በመጨረሻም ፋሲል ድል ሆኖ ሸሽቷል። ራስ ሚካኤል በጭካኔያቸው የጎንደር ሕዝብ ስለጠላቸው ንጉሡን ይዘው ወደ ትግራይ ሔዱ። ራሳቸውን ባለሙሉ ሥልጣንና እንደራሴ አድርገው የበላይ ሆኑ።



ቋጂ.ራስ ሚካኤል ሥዑል

በዚህ ጊዜ ጎንደሮች የዐጤ ኢያሱ ብርሃን ሰገድን የልጅ ልጅ ሱስንዮስን አንግሠናል ብለው አዋጅ አናገሩ። ሸሽቶ ወደ ዳሞት የገባው ፋሲልም ይህን በሰማ ጊዜ ሲገሰግስ ጎንደር ገባ። የመንግሥቱንም ሥልጣን ለመያዝ ባሰበ ጊዜ ጎሹ፣ ያየህይራድና የወንድ ወሰን አናስገባም ብለው ለጦርነት ተሰለፉ። በዚህ ጊዜ እነሱን ለመጉዳት ብሎ ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትና ከራስ ሚካኤል ጋር /የቀድሞ ጠላቶቹ ነበሩ/ በአማላጅ ታርቆ አበረ። ይህ እርቅ በነጎሹ ዘንድ ሲሰማ ድንጋጤን ፈጠረ።

ራስ ሚካኤልም ንጉሡን ይዘው ወደ ጎንደር መጡ። በወቅቱ ከዐርባ ሺህ በላይ ሠራዊት አስከትለው ነበር። አዲሱ ነጋሢ ሱስንዮስም ወደ ቋራ ሸሸ። ከሱ ጋር አብረዋል እየተባሉ የተጠቆሙት ሰዎችም በራስ ሚካኤል ሥውል እጅ ተገደሉ።

በ1764 ዓ.ም ወርሐ ግንቦት በያዝ ለቀቅ ስምንት ቀን የፈጀ ጦርነት ከነራስ ጎሹ ጋር አደረጉ። ራስ ሚካኤል በዕድሜያቸው ሽምግልና የተነሳ እየደከመ ስለነበር የነራስ ጎሹን ኃይል መቋቋም አልቻሉም ነበር። እነራስ ጎሹም የበጌምድር፣ የጎጃም፣ የላስታ ሰው አብሮላቸው ስለነበር አሸነፉ። ራስ ሚካኤል ተማርከው እመኪና አምባ ታሰሩ። ንጉሡ ግን ዙፋናቸውን ይዘው ቀጠሉ። ራስ ሚካኤል በእንደራሴነት ከ34 ዓመት በላይ ገዝተው ቆይተው በሻሽ ታንቀው ሞቱ።

ራስ ሚካኤል ሥውል የዘመነ መሳፍንት መሠረቶች ነበሩ። በዚህ አተራረክ መሠረት መሳፍንቱ ዋና ገዢ በመሆን ኢትዮጵያን እስከ ትንሹ ራስ ዐሊ ዘመን ማለትም ቴዎድሮስ እስከ ነገሡበትና ዘውድ እስከደፉበት 1845 ዓ.ም ድረስ ለ83 ዓመታት ገዝተዋል። ነገር ግን በደከመ ሥልጣን ይሁን እንጂ ነገሥታቱ በዙፋን ላይ ከመቀመጥ በላይ ድርሻ ነበራቸው። መሉ በመሉ የማይወስኑበት ዘመን የመጣውና ሥልጣናቸውን የተቀሙት በራስ ዐሊ ትልቁ ዘመን ነው።

በራስ ሚካኤል ምትክ ራስ ጐሹ እንደራሴነቱን ያዙ። በዚህ የተነሳ ንጉሡና እንደራሴው ተጋጩ። ንጉሡ ራስ ጎሹን አሰሯቸው። የመታሰራቸው ወሬ ሲሰማ እነደጃች ወንድ ወሰን[120] መጥተው ከታሰሩበት እስር ቤት አስፈቷቸው። በኃይልም ከሥልጣናቸው

[120] - የራስ ካሳ አያት ናቸው። ደጃዝማች ወንድ ወሰን ከራስ ጎሹ ጋር ሆነው ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን ይዘው በሥልጣኑ እንዳሻቸው ሲሆኑ የነበሩትን ራስ ሚካኤል ሥውልን ድል አድርገው ከማረኳቸው በኋላ እሳቸውን ከእመኪና አምባ አስፈቷቸው። ንጉሡን ግን በዙፋናቸው አቆይተው በራስ ሚካኤል ምትክ ራስ ጎሹ በታውን

መለሷቸው። ከዚህ በኋላ ተክለ ሃይማኖትን ከዙፋናቸው አወረዷቸው። በግዞትም ወደ ዋልድባ ገዳም ላኳቸው።

መናኙ ዐጤ ተክለ ሃይማኖት

❖ ዐጤ ተክለ ሃይማኖት መናኔ መንግሥት በሚል ቅጥያ ስም ይታወቃሉ። ይህን ቅጥያ ስም ያገኙት ምንም እንኳን ነገሩ በግዞት ቢሆንም መንግሥትን ከለቀቁ በኋላ በታላቁ ገዳም በዋልድባ ሰቋር /አብረንታት ነው የሚሉ ድርሳናት አሉ።/ ዓለም በቃኝ ብለው በመቀመጣቸው የተነሳ ነው። ንጉሡ በመንበረ መንግሥቱ የተቀመጡት ለ7 ዓመታት ሲሆን ዘመኑም ከ1763-1770 ዓ.ም ነው። የነገሡት አንድ ዓመት ብቻ ነግሠው ከሞቱት አባታቸው ዳግማዊ ዐጤ ዮሐንስ /አንድ እጃቸው ቆራጣ በመሆኑ አንድ እጁ በሚል ቅጽል ስም ይጠራሉ።/ ቀጥለው ነው። ተክለ ሃይማኖት ሲነግሡ ዕድሜያቸው ገና 15 ዓመት ነበር። ያነገሧቸውም ራስ ሚካኤል ሲሆኑ ስመ መንግሥታቸው ኃያል ሰገድ ተብሏል።

ንጉሡ የመንግሥትን አስተዳደር ከመንፈሳዊ ተግባር ጋር አጣምረው የያዙና ያስኬዱ እንደነበር ታሪክ ይመሰክርላቸዋል። በመሆኑም አብያተ ክርስቲያናትን ከመትከል፤ ሊቃውንትን ከማሰባሰብና ከመርዳት፤ መጽሐፍትን ከማስተርጎምና ከማጻፍ በሻገር በጾምና በጸሎት ተወስነው ይኖሩ ነበር። ከሁሉ ይልቅ የሚወራላቸው አንድ ተግባር አለ። ይኸውም በቤተ መንግሥታቸው ያሉትን የወርቅ ሠሪዎች አለቃ ጠርተው "ጌታችን ከተቀበለው ጸዋትወ መከራ መቀበል እፈልጋለሁ። ከጫማዬ ውስጥ የብረት ቀኖት ላድርግ ወይስ የብረት ዝናር አሠርቼ ላገልግል" ብለው ያማክሩታል። እሱም ሁለተኛውን አማራጭ ቢጠቀሙ የተሻለ እንደሆነ ስለገለጸላቸው ዝናሩን በፍጥነት ሠርቶ እንዲያመጣላቸው አዘዙት። በትዕዛዙም መሠረት የእሾህ ዝናር ሠርቶ አቀረበላቸውና ያንን መታጠቅ ጀመሩ።

አንዳንድ ድርሳናት እንደሚተርኩት ከሆነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ዋልድባ ገዳም የሔዱት ቅድስት ድንግል ማርያም ተገልጻላቸው "ከቤተ መንግሥት

እንዲይዙ አደረጓቸው። እንግዲህ ደጃዝማች ወሰን ሰገድ ማለት እኚህ ለራስ ሚካኤልና ኋላም ለንጉሡ ከሥልጣን መውረድ ትልቁን ሚና የተጫወቱት ሰው ናቸው።

ወጥተህ እኔ ወደማሳይህ ቦታ በስውር ሒድ" ብላቸው ነው ይላሉ። ይህ አተራረክ ከእውታው ጋር ይጣረሳል። ምክንያቱም ንጉሡ ከመንግሥታቸው የተለዩት በግዞት ነውና። ግዞት ማለት እስር ማለት ነው። እንደአገራችን እውነታ ከሆነ የእስር ቦታ ደግሞ በታሳሪው ፍላጎት ሳይሆን በአሳሪው ፍላጎትና ውሳኔ ነው የሚመረጠው።

ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት በዋልድባ ሳቋር ወደተባለው ገዳም ከተላኩ በኋላ በመምህር አውሴ እጅ ሥርዓተ ምንኩስና ተፈጽሞላቸው መንኩሰዋል። በዋልድባም ጥቂት ጊዜ ቆይተው[121] በ1770 ዓ.ም ሞተዋል። ንጉሡ አባ ሚናስ በተባለው ገዳም ቀብራቸው ከተፈጸመ በኋላ ከምሽቱ ዐሥራ ሁለት ሠዓት እስከ ንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሠዓት ድረስ በመቃብራቸው ላይ ብርሃን ታይቷል የሚል ትርክት አለ።

ተክለ ሃይማኖት ከመሞታቸው በፊት በመንበረ መንግሥታቸው ላይ ሳሉ የጎንደር ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንን ተክለው መቶ ሀምሳ ደብተራዎችን መድበውለት ነበር። የቤተ ክርስቲያኑ ቦታ የሚገኘው በደርግ መንግሥት የጎንደር ከተማ አስተዳዳሪ የነበሩት ሻለቃ መላኩ መኖሪያ ግቢ ውስጥ ነው።

ደርቡሽ ጎንደርን በወረረበት ጊዜ ከተቃጠሉትና ከወደሙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዱ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ነው። ፅላቱ በዚያው በጎንደር ከተማ በበዓታ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ በደባልነት ይገኛል። የአስተዳዳሪው ስመ ማዕረግ "አለቃ" ይሰኝ ነበር።

ምንጭ

- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ገጽ 28፣ 295፣ 296
- ዝክረ ሊቃውንት። ገጽ 50-53

[121] - አንድ ዓመት ከስድስት ወር በገዳሙ እንደቆዩ የሚገልጹ ድርሳናት አሉ። /ዝክረ ሊቃውንት። ገጽ 52/ ነገር ግን ዋልድባ ይህን ያህል ዓመት ቆይተዋል ማለት በመንበረ መንግሥቱ ከቆዩበት ዘመን ጋር ይጣረሳል። በዚሁ መጽሐፍ ላይ ከመቼ እስከመቼ እንደሆነ ባይገለጽም በመንግሥቱ ላይ 7 ዓመት መቆየታቸው ተተርኳል። በመሆኑም በዋልድባ 18 ወራትን ተቀምጠዋል የምንል ከሆነ በመንበሩ የነበራቸው ቆይታ 5 ዓመት ከ6 ወርን የዘለለ አይሆንም። ምክንያቱም ንጉሡ ከ1763 — 1770 ዓ.ም ነው የነገሡት። የሕይወት ዘመናቸውም ፍጻሜ መንግሥትን በለቀቁበት ዓመት 1770 ነው።

- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ። ገጽ 284 — 287
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ። ገጽ 63

26.ሠለስቱ ምዕት ቤተ ክርስቲያን

ሠለስቱ ምዕት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ በ318ቱ ሊቃውንት ስም የተመሠረተ ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት በጎንደር ከተማ ነው የሚገኘው። ከጎንደር ውጪ በየትኛውም የአገራችን አካባቢ አይገኝም። ቤተ ክርስቲያኑ ከዐጤ ፋሲል ቤተ መንግሥት ሰሜናዊ አቅጣጫ በሚገኘው ኮረብታማ ቦታ ላይ የተተከለ ነበር። በቦታው ዛሬ ቤተ ክርስቲያን የለም።

የሠለስቱ ምዕት ጉባኤ ቤት የመጽሐፈ መነኮሳት መምህር የሆኑት ልበ ብሩሀ መምህር ተሾመ ታደሰ ካሳ የካቲት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ለዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ግን ቤተ ክርስቲያኑ ዛሬም አለ ብለዋል። አለ ማለታቸው ከተቃጠለበት ዘመን ጀምሮ ማንም የማሉ ሳያደርገው በመቆየቱና በቦታው ያሉት ሰባቱ የዕድ ዛፎች ያለውን ታሪክ በመዘከር የቤተ ክርስቲያን ንብረት መሆኑን እየመሰከሩ በመኖራቸው ነው።



ሻጌበቅጽረ ግቢው ውስጥ ያሉት የጽድ ዛፎችና የነዋሪዎች ቤት

እንደመምህር ተሾመ ገለፃ ከሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የተቃጠለው ደርቡሾች ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ዐጤ ዮሐንስን መተማ ላይ ተዋግተው መጋቢት አንድ ቀን አቁስለዋቸው በነበረበትና መጋቢት 2 ቀን ቁስለኛውን ንጉሥ ይዘው በማፈግፈግ ላይ ያሉት

የንጉሡን ወታደሮች በክፍቱት ጦርነት ጥቃት አድርሰውባቸው ንጉሡን ከገደሉና አንገታቸውን ከቆረጡ በኋላ በ1881 ዓ.ም ነው። በዚሁ ዓመትም ገብኤ ቤቱ በደርቡሾች መቃጠሉን ይተርካሉ። በጽሑፍ የሰፈሩ ሌሎች መረጃዎች እንደሚተርኩት ደግሞ ቤተ ክርስቲያኑ በመጀመሪያው ወረራ ጊዜ /የመጀመሪያው የደርቡሽ ወረራ ጥር 10/ 1880 ዓ.ም ነበር/ ተቃጥሏል።

"ወራሪው የደርቡሽ ጦር በ1880 ዓ.ም በጥር 10 ቀን ጎንደርን ወርሮ አብያተ ክርስቲያናትን አቃጥሎ ካህናትን በሰይፍ ገድሎ ቅርስ አልባ አድርጓት በነበረ ጊዜ ይህ የሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያንም ተቃጥሎ ሙሉ በሙሉ ወድሟል።..."

/<u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u>። ዝኒ ከማሁ ገጽ 174/

በዚህ አንቀፅ አተራረክ መሠረት ሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን የተቃጠለው በመጀመሪያው ወረራ ነው። ተክለ ጻድቅ መኩሪያም <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጤ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ</u> በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ 66 እንዲሁም <u>ዐፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት</u> በተሰኘው ሌላው መጽሐፋቸው ገጽ 448 እና 449 ላይ በዚህ በመጀመሪያው ወረራ ጎንደር ተቃጥላለች፣ በቃጠሎውም 44ቱ የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት መቃጠላቸውን ይተርካሉ። ይህ አተራረክ በቀሲስ ከፍያለው መራሒ <u>ምንትዋብ</u> መጽሐፍ ገጽ 15 ላይ ተደግሟል። ቀሲስ በዚሁ መጽሐፋቸው ገጽ 8 ላይ እቴጌ ምንትዋብ ያሠሯት ቤተ ክርስቲያን /ቁስቋም ማርያም/ በደርቡሽ አለመቃጠሏን ይተርካሉ። የመጽሐፉ አዘጋጅ የካቲት 5 ቀን 2004 ዓ.ም ከዲያቆን መሉቀን ብርሃኑ ጋር ባደረገው ቃለ መጠይቅ በደርቡሾች የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት 42 መሆናቸውን ተረድቷል። ነገር ግን አንዳንድ ድርሳናት እንደሚተርኩት ከሆነ ሳይቃጠሉ የቀሩት አብያተ ክርስቲያናት 4 ናቸው።

ደርቡሾች ለሁለተኛ ጊዜ ጎንደር ገብተው ጥፋት ያደረሱት መጋቢት 2 ቀን 1881 ዓ.ም ዐጤ ዮሐንስን ከገደሉ በኋላ ነው። ምናልባት መምህር ተሾመ ታደሰ በዚህ በሁለተኛው ወረራ ተቃጠለ ያሉት አብነት ትምህርት ቤቱን ሊሆን ይችላል።

ቤተ ክርስቲያኗ ጥር 10 ቀን ከተቃጠለችና ከተዘረፈች በኋላ ከላይ ያለው ታሪካና የታላላቅ ሊቃውንት መናገሻ የመሆኗ ነገር አብቅቶላታል። ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት

ሲታደሱ ሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን የመታደስ ዕድል አላገኘችም። ታቦቱ ግን በአጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በደባልነት ገብቶ እየተገለገለ ይኖራል።


የሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን *ሐመረ ኖኅ* ይባል ነበር። ሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን የተተከለችው በ1770 ዓ.ም ሲሆን ተካይዋም የቀዳማዊ ዮሐንስ ልጅ ዐጤ ቴዎፍሎስ ናቸው። ቴዎፍሎስ *ሥልጣነ መንግሥትን* የያዙት ከወንድማቸው ከአድያም ሰገድ ኢያሱ ልጅ ከዐጤ ተክለ ሃይማኖት ቀጥሎ ነው። ያነገሧቸውም ከእሳቸው ቀጥሎ *ሥልጣነ መንግሥቱን* ለመያዝ የበቁት /በወቅቱ በጅሮንድ ኋላ ራስ የተባሉት/ ዐጤ ዮስጦስ ነበሩ። ቤተ ክርስቲያኑን ያሠሩት በሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ ሊቃውንት ስም ነው። የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ስመ ማዕረግ መልአከ ሰላም ይሰኛል።

ዐጤ ቴዎፍሎስ ቤተ ክርስቲያኑን ከተከሉ በኋላ ደብሩን የሚያገለግሉ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት ሊቃውንት መድበዋል። የእነዚህ አገልጋዮች ቁጥር ወደ ዐራት መቶ ሃምሳ ያደገበት ወቅት ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው። የትልቁ ራስ ዐሊ[122] እናት ወ/ሮ መነን ከሮሐ /ከቅዱስ ላሊበላ/ አፈር በበቅሎ አስጭነው በማምጣት ቤተ መቅደሱን ይደለድላሉ። በመቀጠልም በተደለደለው ቤተ መቅደስም ላይ መንበሩ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ። ከዚህ በኋላ ሕዝበ ክርስቲያኑን ከጽኑ ደዌ የሚፈውስ ፀበል ይፈልቃል። ፀበሉ የፈለቀው ከቤተ ክርስቲያኑ ዝቅ ብሎ ሲሆን የቅዱስ ላሊበላ ፀበል ነበር። የመስፍኑ እናት ይህን ባዩ ጊዜ የቦታውን ታላቅነት አክብረው ቀድሞ ካሉት 318ቱ ሊቃውንት በተጨማሪ 132 ሊቃውንት በማከል ቁጥሩ 450 እንዲደርስ አድርገውታል።

የሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን ይዞታ የሆነው ቦታ እስከዛሬ ድረስ የማንም ይዞታ ሳይሆን ቆይቷል። ግቢው የቀበሌ ጽሕፈት ቤት ሆኖ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። መቅደሱ ግን በፋሽስት ጣሊያን ከተቀመጠበት የውኃ ታንከር በቀር ምንም የለበትም። በእርግጥ እልፍ ብሎ የከተማዋ ነዋሪዎች ቤት አለ። ከዚህ ሌላ ቦታው የቤተ ክርስቲያን እንደሆነ የሚጠቁሙ ቅርሶች አሉ። እነዚህ ቅርሶች ዛፎች ናቸው። ዛፎቹ በቁጥር ሰባት ሲሆኑ ሁሉም የፅድ ዛፎች ናቸው።

[122] አባታቸው ሴሩ ጓንጉል ናቸው። እናታቸው ደግሞ ወ/ሮ ገለቡ ፋሬስ ናቸው። ስለሙ በዙፋኑ በሚቀመጡት ነገሥታቶች ከለላ ሆነው በዋና አስተዳዳሪነት ከ1777-1781 ዓ.ም ለዐራት ዓመታት ያህል ቆይተዋል። ስረ መሠረታቸው ከሼህ ዑመር ነው። ሼህ ዑመር የባሕር ማዶ ሰው ሲሆኑ የመጡበትም ጊዜም 1515 ዓ.ም በኢማም አሕመድ ዘመን ነው። ሼሁ እንደመጡ የሰፈሩት በየጁ ነው። በየጁም ብዙ ሚስቶች አግብተው ብዙ ልጆችን ለመውለድ በቅተዋል። ከሼህ ዑመር እስከ ራስ ዐሊ ትልቁ ድረስ አምስት ትውልድ አለ። ግልፅ ለማድረግ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ይቀመጣል። <u>ሼህ ዑመር</u> ወሌ፣ አብዬ፣ ወሌ፣ አባ ገትዬ፣ ሴሩ ጓንጉል፣ <u>ራስ ዐሊ</u> ትልቁ። የተሰመረባቸው ሁለቱ መነሻና መድረሻ በመሆናቸው ነው።

ዲያቆን ሙሉቀን እና መምህር ተሾመ እንደሚገልጹት ከሆነ ቦታው የቤተ ክርስቲያኗ ንብረት መሆኑን ለማስወሰን በሕግ በኩል ለተጀመረው ሒደት ዐቢይ ምስክር ሆነው የተገኙት እነዚህ ሰባት ዕድሜ ጠገብ የዕድ ዛፎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ሲተከል ዛፍ መትከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባሕል መሆኑን በመግለጽ የእነዚህ ዛፎችም መኖር ይህንን እንደሚገልጽም እንደ አንድ መከራከሪያ ነጥብና ዐቢይ ማስረጃ ሆኖ ቀርቧል።



ግቯ.በቤተ መቅደሱ ላይ ተቀምጦ የሚገኘው የውኃ ታንከር

መምህር ተሾመ እንደገለፁት ከሆነ ቦታው በጣሊያን የወረራ ዘመን የወታደር ካምፕ ሆኖ ነበር። ፋሽስቶች ከወጡ በኋላም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ወታደሮች ይኖሩበት ነበር። በደርግም ዘመን እግዚአብሔር በጥበቡ እየጠበቀው ስለቆየ በየትኛውም የመንግሥት ሥርዓት ለማንም አልተሰጠም። ከቅጽረ ግቢው ውጪ በቤተ ክርስቲያኑ ስር ያለ ጉባኤ ቤት አለ። መምህር ተሾመ የዚህ ጉባኤ የወቅቱ የመጽሐፈ መነኮሳት መምህር ናቸው።

ጉባኤ ቤቱ የተመሠረተው ከዛሬ 337 ዓመታት በፊት ከቤተ ክርስቲያኑ እኩል በ1770 ዓ.ም ነው። በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኗን የተከሉት ዐጤ ቴዎፍሎስ ገና ዙፋን አልያዙም ነበር። ጉባኤ ቤቱ ለረጅም ዓመት አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቶ በ2004 ዓ.ም ለሁለተኛ ጊዜ የእሳት ቃጠሎ አደጋ ደርሶበት ከነመማሪያና ማስተማሪያ ግብዓቶቹ ጭምር ወድሟል። ቃጠሎው የተከሰተው የካቲት 7/ 2004 ዓ.ም ሲሆን መንስኤው ምን እንደሆነ አልታወቀም። ሠዓቱ ከምሽቱ ዐሥራ አንድ ሠዓት ስለነበር ጉባኤው ተጠናቆ ደቀ መዛሙርቱም ተበትነዋል። መምህሩ ደግሞ ተኝተው ነበር። መምህሩን ከቃጠሎው ያተረፏቸው የጉባኤ ቤቱን መቃጠል ያዩ ሰዎች መጥተው አውጥተዋቸው ነው።

መምህር ተሾመ ታደሰ

❖ መምህር ተሾመ ውልደታቸው ፀሰምት ነው። ከዛሬ ስድሳ ሰባት ዓመታት በፊት 1940ዎቹ መጀመሪያ ላይ ነው የተወለዱት። አባታቸው ታደሰ ካሣ ይባላሉ። መምህር ተሾመ የዓይን ብርሃናቸውን ያጡት በልጅነታቸው ነው። ይህ ዓይነቱ ችግር የተከተሰተባቸው በአንድ የሠርግ ድግስ ወቅት ሲሆን ተሾመ የድግሱን ወጥ ውሻ እንዳይለክፈው ጠበቅ ተብለው ይታዘዛሉ። ሙሉ ቀን ዓይናቸውን ከድስቱ ላይ ሳይነቅሉ ይውላሉ። የፀሐይ ነፀብራቅም ሳይበግራቸው ትዕዛዛቸውን ለመፈጸም በዚሁ መልኩ ይቀጥላሉ። ምሽት ላይ ዓይናቸው ተከለለ። ሌሊቱን በስቃይ አሳልፈው ሲነጋ ተወት አደረጋቸው። ለሳምንታት ያህል እፎይ ብለው እንደቆዩ እንደገና አገረሸባቸው። ክፉኛ ውጋት ይሰማቸው ጀመር። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ለድፍን ዘጠኝ ወራት ያህል ከዓይናቸው ደምና መግል ፈሰሰ። ብሶባቸውም በአልጋ ዋሉ። በዘጠነኛው ወር ጠዋት የግራ ዓይናቸው፣ ማታ ደግሞ የቀኝ ዓይናቸው ጠፋ።



ሥዕ. መምህር ተሾመ ታደሰ

መምህር ተሾመ በወቅቱ የባሕል መድኃኒት ተጠቅመው ነበር። መድኃኒቱ አዘዛር የተባለ እንጨት ነበር። ይህን እንጨት ቤተሰቦቻቸው ቀጥቅጠው በቀሏቸው ጊዜ ፊታቸው ተላላጠ። ይባስ ብሎም ፀጉራቸው ረገፈ። ፀጉራቸው መብቀል የጀመረው ጎንደር መጥተው በዘመናዊ ሕክምና በክኒንና በመርፌ ሕክምና አግኝተው ነው። ነገር ግን ሕክምናው የዓይናቸውን ብርሃን ሊመልስላቸው አልቻለም። የያኔው ታዳጊ በተለያዩ የአብነት ትምህርት ቤት እየተዘዋወሩ ዜማ፣ ቅኔ፣ አቋቋም፣

ተማሩ። በመቀጠልም ከመምህር ኃይለ ሥላሴ ዘንድ መጽሐፈ መነኮሳት መማር ጀመሩ። ሐዲሳትንም ከመምህር ገብረ ሥላሴ ተማሩ።

በሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምእት ገባኤ ቤት ቀድሞ ዐራቱ ገባኤያት ማለትም መጽሐፈ መነኮሳት፣ መጽሐፈ ሐዲሳት፣ መጽሐፈ ብሉያት፣ መጽሐፈ ሊቃውንት ይሰጡበት ነበር። ነገር ግን በ1969 ዓ.ም ክቡር ዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ ሲሞቱ በወቅቱ በነበሩት መምህራን ፍላጎት መሠረት መጽሐፈ መነኮሳትና መጽሐፈ ሊቃውንት ለየብቻቸው እንዲሰጡ ሆኗል። በዚህም መሠረት መምህር ኃይለ ሥላሴ መጽሐፈ መነኮሳትን ይዘው በሐመረ ኖኅ ሲቀጥሉ ሊቀ ሊቃውንት መንክር ደግሞ መጽሐፈ ሊቃውንት በመንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ማስተማር ጀመሩ። ይህ የሆነው በጳጳሱ በአቡነ እንድርያስ ውሳኔ ነበር።

በዚህ ገባኤ ቤት ስመ ጥር የሆኑ ታላላቅ ሊቃውንት አስተምረውበታል። ከእነዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ብቸኛው እና የመጀመሪያው የክብር ዶክትሬት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተሰጣቸው ሊቅ አለቃ አየለ ዓለሙ ቀዳሚው ናቸው።

ክቡር ዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ

- አለቃ አየለ ዓለሙ የተወለዱት ቀድሞ በጎንደር ጭልጋ አውራጃ በዳዋ ወረዳ ይባና ማርያም በተባለ ቦታ ነው። ዘመኑ ደግሞ 1867 ዓ.ም አባታቸው አቶ ዓለሙ ኪዳነ ማርያም ይባላሉ። እናታቸው ደግሞ ወይዘሮ ማንአህሎሽ ወልደ ጊዮርጊስ። ወይዘሮ ማንአህሎሽ ባላቸው አቶ ዓለሙ ሲሞቱባቸው ሕጻኑን ይዘው ወደ ትውልድ መንደራቸው ገንዳዋ ገብርኤል ይዘዋቸው ይሔዳሉ። ብላቴናው አየለ ወደ እናታቸው አገር ከመሔዳቸው በፊት ከትውልድ ቀያቸው አበ ገዳም ከመሪጌታ ሣህሌ ዘንድ ትምህርት ጀምረው ነበር። እስከ ዳዊትም ደርሰዋል። ወደ እናታቸው መንደር ከሔዱ በኋላ አለቃ አበራ የተባሉት አጎታቸው እናታቸውን አስፈቅደው ብላቴናውን ወደ ጎንደር አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ይዘዋቸው ሄዱ።

አለቃ አበራ የድጓ መምህር ሲሆኑ አየለ በአእምሮ እስኪበሰሉ ድረስ ከእርሳቸው ጋር አቆይተዋቸዋል። ድጓንም አስተምረዋቸዋል። ታዳጊው አየለ በዚህ ቦታ በዜማ ትምህርት እጅግ የተደነቁ ሆነው ነበር። ፍላቱ የሚል ቀጽል ስምም

ተሰጥቷቸዋል። የቅኔ ትምህርትን መማር የፈለጉት አየለ ከአጎታቸው ፍቃድ ጠይቀው ወደ ደንቢያ ዓራቢያ መድኃኔ ዓለም ሐይደው ቅኔ መቅሰም ጀመሩ። የፈለጉት የቅኔ ትምህርት እንደፍላጎታቸው አልሆነላቸውም። ከበዳቸው። ተስፋ ቆርጠው ወደመጡበት ተመለሱ። ይህን የሰሙት የቅኔ መምህራቸው መምህር አባተ "ሂዱና ድርማን ሳይሻገር ያገኛችሁት እንደሆነ እንደምንም ብላችሁ ይዛችሁት ኑ፤ ወንዙን ተሻግሮ ካገኛችሁት ግን ተውት" ብለው ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ይልኩባቸዋል። ደቀ መዛሙርቱም ሳይሻገሩ ስላገኟቸው ይዘዋቸው ይመለሳሉ። በመጨረሻም በቅኔ ዘራፊነታቸው አሉ የተባሉ ሊቅ ሆነዋል።

በመቀጠልም በአጎታቸው ላኪነት ዜማን አጠናቀው እንዲመረቁ ወደ ቤተልሔም ልከዋቸው እየተማሩ ሳለ አለቃ ጎሩይ ፊንታ የተባሉ የመጽሐፍ መምህር ጥሪ አደረጉላቸው። ከእሳቸውም የመጽሐፍ ትርጓሜን /የቁርሶስ ትርጓሜን/ አጠኑ። ቀጥለውም ወደ ጎጃም ደምበጫ ቅዱስ ሚካኤል ሐይደው ከአለቃ ተስፋ ዘንድ የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ ተማሩ። አለቃ ተስፋ ወደ ሞጣ ሲቀየሩ ተከትለዋቸው በመሐይድ የመጽሐፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ጠነቀቁ። መምህርነታቸውንም አስመስክረው ወደ ጎንደር ተመለሱ።

አለቃ አየለ በጎንደር ግምጃ ቤት ማርያም ከመምህር ተክለ ማርያም ቀጥሎውም ወደ ደረስኔ ማርያም ከመምህር ገብረ ማርያም ዘንድ ሐይደው መጽሐፈ ሐዲሳትን አሄዱ። ይህን ከጨረሱ በኋላ ወደ ጎንደር ተመልሰው ከአለቃ ዘዮሐንስ ዘንድ የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ቀጠሉ። በዚህ ጊዜ ጎን ለጎን መጽሐፍት ሊቃውንትን ማስተማር ጀምረው ነበር። ከዚህ በኋላም ከመምህር ሣህሌ ወልደ ተክሌ መርሐ ዕውርንና አቡሻኽርን ተማሩ። በዚህ እውቀታቸውም የዐራቱ ጉባኤያት መጽሐፍትን ከነትርጓሜያቸው፤ የአቡሻኽርን መጽሐፍ ከነሰንጠረዡ ጽፈዋል።

አለቃ በ1916 ዓ.ም ከመንግሥት በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ወደ አዲስ አበባ ከአለቃ ጎሩይ ፊንታ ጋር መጡ። ከሌሎች ሊቃውንት ጋር በመሆን /ሁለቱም/ መጽሐፍትን ማስተማር ብሎም የሚታተሙ መጽሐፍቶችንም ማዘጋጀትና ማሳተም ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ እያሉ የላሊበላ ገዳማት መምህር ከሆኑት ከመምህር ጎሩይ መጽሐፍተ መነኮሳትን፤ ከመምህር ፍላታዎስ መጽሐፍተ ብሉያትን አጠኑ።

ከመምህር ገሪማ /የኋላው አቡነ ሚካኤል/ ዘንድ ዐሥራ ዐራቱን ቅዳሴያት ተምረው አጠናቀቁ። ለረጅም ጊዜያትም ዐራቱን ጉባኤያት በአዲስ አበባ ሲያስተምሩ ቆዩ።

ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን ወርሮ በነበረበት ወቅት በአብርሃ ደቦጭና በሞገስ አስገዶም ለተሰነዘረው ጥቃት የበቀል አጸፋ እንዲሆን በፊሽስት በተደገሰው የየካቲት 12ቱ ጭፍጨፋ ጊዜ ከነደቀ መዛሙርታቸው ለ9 ቀን ያህል አሰሯቸዋል። ከነፃነት በኋላ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ባስሊዮስ የጎንደር በዓታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን አለቃ አድርገው ሾሟቸውና ጎንደር ገቡ። ዐራቱን ጉባኤያት ዘርግተውም ማስተማር ጀመሩ።

የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ከሰጣቸው ቀደምት ሰዎቻችን መሐከል አንዱ አለቃ አየለ ናቸው። ማዕረጉ የተሰጣቸው በሰኔ 1960 ዓ.ም ነበር። በዚህ ጊዜ የሊቃውንት ኮከብ ተብለዋል።

አለቃ ክቡር ዶክተር አየለ ዓለሙ በትህትናቸውና በርኅራኄያቸው ብዙዎች ያውቋቸዋል። ከንጉሡ የሚሰጣቸውን ቀለብ እየተቀበሉ በወቅቱ ከሳቸው ዘንድ የሚማሩትን ደቀ መዝሙራት ይመግቡ ነበር። በዚህም የተነሣ ብዙ ተማሪዎች ወደ እሳቸው ይመጡላቸው ነበር። ዘመናቸውን ሙሉ በመማር፣ በማስተማርና እግዚአብሔርን በማመስገን ሲተጉ ኖረው በአንድ መቶ ሁለት ዓመት ዕድሜያቸው በጥር 16/1969 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። አስከሬናቸው በመንበረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር አርፏል።

ክክቡር ዶክተር አየለ ዓለሙ ሕልፈተ ሕይወት በመቀጠል መምህር ኃይለ ሥላሴ ወልደ ሚካኤል እስከ 1987 ዓ.ም በሠለስቱ ምእት የመጽሐፈ መነኮሳት ወንበር ዘርግተው አስተማሩ። መምህሩ ኤርትራዊ በመሆናቸው ኤርትራዊያን ከአገር እንዲወጡ በታዘዙ ጊዜ ኢትዮጵያን ለቅቀው ወጥተዋል። በእሳቸው ምትክ መምህር ክንፈ ርግብ ተስፋዬ የሚባሉ መምህር ተተክተው ለዐራት ዓመታት አገልግለዋል። አገልግሎታቸው የተቋረጠው ጎዳር 30 ቀን 1991 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት ነው። ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ ግን የአሁኑ መምህር ተሾመ ታደሰ እያስተማሩ ይገኛሉ።

መምህር ተሾመ የካቲት 7 ቀን 2004 ዓ.ም ጉባኤ ቤታቸው እስከተቃጠለባቸው ጊዜ ድረስ በቋሚነት ስምንት፤ በተመላላሽነት ዐሥር ደቀ መዛሙርት ነበሯቸው። ጉባኤ ቤቱን መልሶ ለማቋቋምና ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ ሕዝበ ክርስቲያኑ መረባረብ እንዳለበትም ገልፀዋል። ስለጉባኤ ቤቱ "ነበር ከማለት አለ ማለት መልካም ነው" ይላሉ። የሠለስቱ ምእት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን የመጽሐፈ መነኮሳትም ብቸኛው መገኛ ጎንደር ነው። ከጎንደርም ታሪኩ እንዲህ በተተረከለት በእሳት በወደመው እና የቀበሌ ጽሕፈት ቤት አገልግሎት እየሰጠ በሚገኘው ቦታ። የሠለስቱ ምእት የመጽሐፍተ መነኮሳት አብነት ትምህርት ቤት ለማሠራት የመሠረት ድንጋይ የተጣለ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ ያለበት ይዞታ ለማስመለስ ጥረት እየተደረገ ነው።

ምንጭ

- የእውቀት አፍላጋት ቀ.1 ዘጋቢ ፊልም። ታኅሣሥ 2004 ዓ.ም
- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ዝኒ ከማሁ ገጽ 73፣77፣174፣175
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐጤ ቴዎድሮስ እስከ ኃይለ ሥላሴ። ዝኒ ከማሁ ገጽ 66
- ተክለ ጻድቅ መኩሪያ ዝኒ ከማሁ ገጽ 448፣450
- ትዕግስት ታፈረ። የአብርሃም ቤት ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ቅጽ 1ኛ ቁጥር 2004 ግንቦት 1-15/2004። ገጽ 8-9
- መምህር ተሾመ ታደሰ። ቃለ መጠይቅ። የካቲት 15/2004
- ዲያቆን መሉቀን ብርሃኑ። ቃለ መጠይቅ። የካቲት 15/2004
- መሠረት ከበደ። የማኅበረ ቅዱሳን የመጽሐፍት ዝግጅት ክፍል። ፍሬ ሊቃውንት አዲስ አበባ። 1999 ዓ.ም ከገጽ 13-21
- የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ። ዝኒ ከማሁ። ገጽ 44፣45
- ከፍያለው መራሒ። ምንትዋብ። ንግድ ማተሚያ ድርጅት ገጽ 8፣15
- ዝክረ ሊቃውንት ካልዕ። ገጽ 337-339

27. ጨጊ ቅድስት ማርያም ገዳም

ጨጊ ቅድስት ማርያም ገዳም መገኛዋ በሰሜን ጎንደር አገረ ስብከት በኮሳየ ወረዳ /ጨረማ ወረዳ/ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ የታነጸችው በዐጤ ይስሐቅ ዘመነ መንግሥት /ከ1399 - 1414 ዓ.ም/ ነው።

ዐጤ ይስሐቅ

- አባቱ ዐጤ ዳዊት ሲሆን መንበረ መንግሥቱን የያዘው ከ1395 — 1399 ዓ.ም ለዐራት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ ተቀምጦ ሲያስተዳድር ከቆየውና በ1399 ዓ.ም በተፈጥሮ ሕመም ምክንያት አማራ ሣይንት ሰኔ 29 ቀን አርፎ ከተቀበረው ወንድሙ ከቀዳማዊ ዐጤ ቴዎድሮስ ቀጥሎ ነው።

ዐጤ ይዓሐቅ በተደጋጋሚ ከሙስሊሞች ጋር ጦርነት የገጠመ ሲሆን ሁሉንም በድል አጠናቋል። ሳድአዲን ከተባለው ሰው ጋር ተዋግቶ ድልን ሲቀዳጅ የሳድአዲን ዐሥር ልጆች ወደ ዐረብ አገር ሸሽተው ሔደዋል። በዐረብም በናስር አሕመድ ቤን አሽራፍ ኢስማኤል ቤተ መንግሥት ጥቂት ቆይተው እርዳታ አሰባስበው ተመልሰው መጡ። ከቀድሞው ጦርነት የተረፉት ሙስሊሞች መጥተው አበሩላቸው። በክርስቲያኑ መንግሥት ላይ ጦርነት አስነሱ። የንጉሡ ወታደሮች መሪ ያደረጉትን ወንድማቸውን ገድለው አባረሯቸው። በሞተው መሪ ምትክ ሌላ መርጠው እንደገና ውጊያውን ቀጠሉ። አሁንም በንጉሡ ድል ተደረጉ። በሁለተኛው ጦርነት ላይ ከወንድማማቾቹ መሐከል ሁሉቱ ተማርከው እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በእስር ቤት ቆይተዋል። ሙስሊሞቹ አሁንም ጋማልአዲ የተባለ ወንድማቸውን መሪ አድርገው ጦርነቱን ቀጠሉ። መሪው ከፍተኛ የጀግንነት ሥራ ሠርቶ ንጉሡንና ሠራዊቱን እስከ ዓባይ ወንዝ ድረስ አባርሯቸው ነበር። በመጨረሻ ግን ንጉሡ አንሰራርቶ የመልሶ ማጥቃት ውጊያ በማድረግ ድል አግኝቷል። በሌላ በኩል ደግሞ በዚህ መሪ የተሾመው የጦር አለቃ ሐርብጃዊሽ በያጅዛህ በባሌና በአቅራቢያው ተዋግቶ በማየሉ ምክንያት በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን ያወድም፤ ክርስቲያኖችንም እየማረከ ለባርነት ይሸጥ ነበር።

ንጉሡ ዐጤ ይስሐቅ ከእነዚህ ጋር ብቻ ሳይሆን የአይሁድ እምነት ተከታይ ከሆኑት ፈላሻዎች ጋር ወደ በጌምድር ሔዶ ተዋግቷል። ድልም አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪም በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቷል። ካሠራቸውም መሐከል ደብረ

ይስሐቅ ለአብነት ይጠቀሳል። ሌላው ደግሞ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሊያሠራ የሞከረውና ገንዘባቸውን ለመነኮሳቱ ሰጥቶ ያሠራው ቤተ ክርስቲያን ተጠቃሽ ነው።

ንጉሡ በዘመኑ በደብረ ሊባኖስ ገዳም ውስጥ አንድ ቤተ ክርስቲያን ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገባው ቃል ኪዳን መሠረት ከበረከቱ ለመሳተፍ በፈቃዱ ሠርቶ ነበር። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኑ ማንም ምንም ሳያደርገው በመፍረሱ ምክንያት አዝኖ ማኅበረ መነኮሳቱን በምን ምክንያት እንደፈረሰ ለማወቅ ይጠይቃል። በወቅቱ የነበሩት የገዳሙ እጨጌ በሰባተኛ የእጨጌዎች ተርታ ላይ የሚገኙት እጨጌ ዮሐንስ ከማ ነበሩ።

እጨጌው የንጉሡን ጥያቄ ተቀብለው በዓታቸውን ዘግተው ወደ ተቀመጡ ባሕታዊ በመሔድ የዚህን ምሥጢር ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ ያገኙትን መልስ እንዲያሳውቋቸው ያሳስቧቸዋል። ባሕታዊውም ባገኙት መልስ መሠረት ንጉሡ ያልተፈቀደለት መሆኑን ነገር ግን መነኮሳቱ ቢሠሩት ቤተ ክርስቲያኑ እንደሚጸና ይገልጻሉ። ዐጤው ይህን በሰሙ ጊዜ ለመነኮሳቱ ገንዘብ ሰጥተው ቤተ ክርስቲያኑ እንዲሠራ ያደርጋል። ሥራው ሰባት ዓመት ፈጅቶ ሲጠናቀቅ ንጉሡ በገዳሙ ተገኝቶ በርካታ ንዋያተ ቅድሳት ሰጥቷል።

ዐጤ ይስሐቅ በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ ከ1399 -1414 ዓ.ም-ለዐሥራ አምስት ዓመታት ያህል ተቀምጦ ከአስተዳደረ በኋላ የግዛት ዘመኑ አብቅቷል። ዘመኑ ያበቃው በሞት ነው።

ዐጤ ሱስንዮስ ካቶሊክ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሃይማኖት መሆኑን ባወጀ ጊዜ ከተቃወሙ አባቶች መሐከል አንዱ የሆኑት አባ ምዕመነ ድንግል፤ ዐርባ የሚሆኑ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስከትለው በመምጣት በጩጊ ማርያም ዋሻ ተቀምጠዋል። የሱስንዮስ ልጅና ሃይማኖት ይመለስ ፋሲል ይንገሥ የተባለለት ዐጤ ፋሲል በእነዚህ አባት የተነሳ ለገዳሚ ሰፊ ርስት ሰጥቷል።

አባ ምዕመነ ድንግል

- እነዚህ አባት ቀድሞ የዋልድባ ገዳም መምህር ነበሩ። የተወለዱት ሰሜን ጎንደር ወገራ በተሰኘች ቦታ ነው። ገና በብላቴናነት ዕድሜያቸው ነው ነደያንን መመፅወት፤ ድውያንን መፈወስ የጀመሩት። እነዚህ አባት ደባርቅ አዳጋት ቅድስት ማርያም ገዳም ገብተው

የመንፈሳዊ አገልግሎት ተግባራቸውን ጀምረዋል። ኂሳም በአባ ጴዋ ድንግል እጅ ምንኩስናን ተቀብለዋል። ዋልድባ ገዳም የገቡት ከዚህ በመቀጠል ነው። በዋልድባ ለገዳሙ አበምኔትነት ገዳማዊያኑ ሲመርጧቸው ጥለው ጠፍተው የነበረ ቢሆንም ገዳማዊያኑ ፈልገው አምጥተዋቸው በግድ ሾመዋቸዋል።

አባ ምዕመነ ድንግል ከነአባ ዓምደ ሥላሴ /የማኅበረ ሥላሴ ገዳም አበምኔትና አቅኒ/ ጋር ሆነው በጸሎታቸው የንጉሥ ሱስንዮስ አንደበት እንዲናገር አስችለዋል። እኚህ አባት ይህን ከማድረጋቸው በፊት በጨጊ ማርያም ገዳም በዋሻ ውስጥ ነበሩ።

ልዑል ሩሲል አባቱን አድኑልኝ ብሎ ለገዳማዊያን አባቶች በላከ ጊዜ ወደዚህ የመጡ መልዕክተኛ ወታደሮች ነበሩ። እነዚህ ወታደሮች ወደ ዋሻው ሲቀርቡ ከአባ ምዕመነ ድንግል ደቀ መዛሙርት አንዱ ወደ ዋሻው ውሻ መምጣቱን ይነግራቸዋል። ይህን ጊዜ *ውሻ መጣ ሰው መጣ ሰው መጣ ነገር መጣ* ብለው በዋሻው ካለ ትልቅ ባሕር ዘለው ገቡ። ነገር ግን በባሕሩ ያለው ቋጥኝ ከመስጠም አተረፋቸው። ይህን የተመለከቱት ወታደሮች በሁኔታው ተደናግጠው ይዘው የመጡትን ደብዳቤ አሳዩዋቸው። ከዚህ በኋላ ወደ ንጉሡ ዘንድ ሔዱ።

ንጉሡም ድነው *የካቶሊክ ሃይማኖት ትርከሰ* ብለው አዋጅ አናግረዋል። አባ ምዕመነ ድንግል በጨጊ ማርያም ዋሻ ለረጅም ዓመታት በፆም ጸሎትና በፍፁም ብሕትውና ተወስነው ኖረው ሰኔ 21 ቀን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ይህ ዋሻ ዛሬ በስማቸው "ምዕመነ ድንግል ዋሻ" ተብሎ ይጠራል።

ጨጊ ማርያም ገዳም በደርቡሽ የወረራ ዘመን ተቃጥሏል። ከዚህ ቃጠሎው በኋላ በ1926 ዓ.ም እንደገና ተቋቁሞ እየተገለገለ ይገኛል።

ምንጭ

- ዜና ዕበይ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት ኢትዮጵያዊ። ፕሮሚየም ፕላስ ፕሪንተርስ፣ ደብረ ሊባኖስ ገዳም። ገጽ 12
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ይኩኖ አምላክ እስከ ዐፄ ልብነ ድንግል። ገጽ 125፣ 126፣ 127
- የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ። ገጽ 249፣250

- <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u>። ዝኒ ከማሁ። ገጽ 637፣ 638
- <u>የቃል ኪዳን ምድር</u>። ዘጋቢ ፊልም ቁጥር 1

28. <u>አባ እንጦንስ ቤተ ክርስቲያን</u>


አባ እንጦንስ ቤተ ክርስቲያን ጻድቅ እየተባሉ በሚጠሩት ዐጤ ዮሐንስ አንደኛ /በስመ መንግሥታቸው አእላፍ ሰገድ/ ናቸው የተከሉት፤ በጎንደር ከተማ ውስጥ። ቤተ ክርስቲያኑ ከቀሃ ወንዝ በምዕራብ አቅጣጫ ከባሻገር ባለው ተረተር ላይ ነው የተተከለው። የትክል ዘመኑ ደግሞ በንጉሡ የሥልጣን ዘመን እኩሌታ ላይ 1668 ዓ.ም ነው። ፡

በአባ እንጦንስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግሉ መቶ ሃምሳ የሚሆኑ ቀዳስያንና ደብተራዎችን መድበውለት ነበር። ንጉሡ ይህን ቤተ ክርስቲያን ከመሥራታቸው በፊት ጠዳ እግዚአብሔር አብን ተክለው ነበር። የአባ እንጦንስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪም "መልአከ ምሕረት" የሚል ስመ ማዕረግ ነበረው። ቤተ ክርስቲያኑም ደግሞ መካነ ቅዱሳን እንጦንስ ተብሎ ተሰይሟል።

ቀዳማዊ ዐጤ ዮሐንስ

❖ ዐጤ ዮሐንስ አንደኛ /አእላፍ ሰገድ/ አባታቸው በካቶሊክ ሃይማኖት ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ የገባችውን አገር ከአባታቸው ከሱስንዮስ ተቀበለው ለ36 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት ዐጤ ፋሲል ናቸው።

ሥልጣነ መንግሥቱን የተቀበሉት አባታቸው በሞቱበት ዓመት በ1660 ዓ.ም ሲሆን ሲነግሡ ስመ መንግሥታቸው አእላፍ ሰገድ ተብሏል። ንጉሡ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ በመሆናቸው መንበረ መንግሥቱን እንደያዙ ሁሉም በየሃይማኖቱ በያለበት እንዲረጋና ፈረንጆች በአገር እቀመጣለሁ ያሉ እንደሆነ የተዋሕዶን እምነት አምነው እንዲቀበሉና እንዲቀመጡ አውጀዋል። ከዚህም ባሻገር ከአገር ማስተዳደር ሥራ የተረፋቸውን ጊዜ ተዋሕዶዎችንና ቀብዓቶችን በማከራከር ስለሃይማኖት የጠራ ግንዛቤ ለመፍጠር ጥረዋል።



፯. የዐጤ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት

ንጉሡ ዮሐንስ አንድ ሰው፤ ንጉሥም ሆነ ሎሌ ከአንዲት ሚስት በቀር እንዳያገባ የሚደነግግ አዋጅ አውጥተዋል። ብላቴን ጌታ መልአከ ክርስቶስ[123] መንግሥት እንዳይናጋ አገር እንዳይረበሽ ብሎ ዐጤ ፋሲል ሲሞቱ እያደነ በወሕኒ አምባ ያሠራቸውን መኳንቶች ሁሉ እንዲፈቱ /ከነጋሚ ዝርያ ውጪ ያሉትን/ የሚያደርግ አዋጅ አውጀዋል። ይህ የሆነው በመስከረም 27/1661 ዓ.ም ሊቃውንቱና መኳንንቱ ባሉበት ተመክሮ ነው።

ንጉሡ ገና ከልጅነታቸው ጀምሮ በሃይማኖት እየተኮተኮቱ ያደጉ በመሆናቸው መንፈሳዊነታቸው በእጅጉ ያመዝን ነበር። እንዲያውም ባለቤታቸው እቴጌ ሰብለ ወንጌልና የንስሃ አባታቸው ባሉበትና ግብር በተጣለበት በአንዲቷ ቀን "ሦስታችን እውነት ብንናገር ይህ የተጠበሰ ዓሳ በሕይወት ተነስቶ ወደ ባሕሩ ይገባ ነበር" በማለታቸውና ሁሉም እውነት በመናገራቸው የተጠበሰው ዓሳ ተነስቶ ወደ ባሕሩ[124] ገባ የሚል አተራረክ አለ።

ንጉሡ ከ1660 - 1674 ዓ.ም ለዐሥራ ዐራት ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ መንበረ መንግሥት ላይ ሆነው አገሪቷን አስተዳድረው ሐምሌ 5 ቀን 1674 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። የንጉሡ የግዛት ዘመን በአንዳንድ ድርሳናት ላይ 13፤ በሌሎቹ ላይ ደግሞ 15 ዓመታት እንደሆነ ይተረካል።

123 - ኋላ ርዕሰ መኳንንት ብለው የሙሉ እንደራሴነትና ሹመት ሰጥተውታል።
124 - ለዓሳ ማርቢያ ብለው ያዘጋጁት ባሕር እንደነበር ይነገራል።

ቀዳማዊ ዐጤ ዮሐንስ ያሠሩት የአባ አንጦንስ ቤተ ክርስቲያን በደርቡሽ የወረራ ዘመን ተቃጥሏል። በደርቡሽ ከተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያን ውስጥና እስከዛሬ ካልተሠሩት የጎንደር አብያተ ክርስቲያን መሐከል አንደኛው ይህ ቤተ ክርስቲያን ነው።

<u>ምንጭ</u>

- የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት። ቅጽ 7 - ገጽ 138
- <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ።</u> ዝኒ ከማሁ። ከገጽ 159-164
- <u>ዋዜማ</u>። ገጽ 65
- <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u>። ዝኒ ከማሁ ገጽ 292

29- <u>መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ቤተ ክርስቲያን</u>

መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን መገኛዋ በሰሜን ጎንደር በጎንደር ከተማ ነው። ቤተ ክርስቲያኒቱ የተተከለችው በ1650 ዓ.ም ነው። ተካዩዋ ደግሞ ስመ ጥሩው ንጉሥ ዓለም ሰገድ ዐጤ ፋሲል ናቸው።

ዐጤ ፋሲል /ዓለም ሰገድ/

- አባታቸው ሥልጣን ሰገድ ዐጤ ሱስንዮስ ሲሆኑ እናታቸው ደግሞ እቴጌ ወልደ ሠዓላ /ሥልጣን ሞገሳ/ ናቸው። እቴጌይቱ የኦሮሞ የዘር ሐረግ ያላቸው ሴት እንደሆኑ የሚተርኩ ድርሳናት አሉ። ወልደ ሠዓላ ሰሜን ሸዋ መርሐቤቴ በ1653 ዓ.ም አርፈዋል። ሱስንዮስን አግብተው ፋሲልን የወለዱት በሰሜን ሸዋ መንዝ ውስጥ ሲሆን ዘመኑም 1596 ዓ.ም ነው።

  ዐጤ ፋሲል ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በባለውለታነት ከምንፈርጃቸው የጎንደር ነገሥታት መሐከል ቀዳሚው ናቸው። እኚህ ንጉሥ ሥልጣን የተቀበሉት ከአባታቸው ከዐጤ ሱስንዮስ ነው። ሱስንዮስ የካቶሊክ ሃይማኖት ብሔራዊ ሃይማኖት እንዲሆን ባወጁ ጊዜ ከተዋሕዶዎች ጋር

በመወገንና ለተዋሕዶ ሃይማኖት በመቅናታቸው አባታቸውን በግልፅ ተቃውመዋል።

በእርግጥ በወቅቱ ትርምስ ከአባታቸው ጎን ተሰልፈው እንደነበር ታሪክ ይጠቁማል። ልዑሉ ምንም እንኳን ከአባታቸው ወገን ተሰልፈዋል ቢባልም አባታቸውን በግልጽና በተደጋጋሚ ወንድማማች የሆነን ሕዝብ ደም ማፋሰስ ይብቃ ብለዋል። እርግጥ ነው ይህን ሀሳብ እሳቸው ብቻ ሳይሆኑ እህታቸው እቴጌ መለከታዊት ሳይቀሩ በግልጽ እና በአደባባይ ተቃውመዋል። ልዑሉ ኋላም ሲነግሡ "ፋሲል ይንገሥ፣ ኦርቶዶክስ ይመለስ" ተብሎ አዋጅ ተነግሮላቸው ዙፋኑን ለመያዝ የበቁ መሪ ናቸው።

ዐጤ ፋሲል መንበረ መንግሥትን ከአባታቸው የተረከቡት በታኅሣሥ 1623 ዓ.ም አባታቸው ሱስንዮስ ከ1595-1623 ዓ.ም ለ28 ዓመታት ገዝተው ከሞቱ በኋላ ነው። /አንዳንዶቹ ንግሥናቸውን 1625 ዓ.ም ያደርጉታል።/ ሲነግሡ ስመ መንግሥታቸው ዓለም ሰገድ ተሰኝቷል። ንጉሡ የአባታቸው ቤተ መንግሥት ያለበትን ቦታ ከነገሡ ከዐራት ዓመታት በኋላ በመልቀቅ ጎንደር ከተማን በ1628 ዓ.ም የቆረቆሩና ጎንደርን የኢትዮጵያ መናገሻ እንድትሆን መሠረት የጣሉ ናቸው። ግዛታቸውም እስከ ስናርና ኑቢያ ድረስ ይዘልቅ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። በኑቢያም ጊዮርጊስ የተሰኘ ባለሟላቸውን ሾመውበት ነበር።



ፎቶ.የዐጤ ፋሲል ዘመን ተሻጋሪ ቤተ መንግሥት

ዓለም ሰገድ ዐጤ ፋሲል በኢትዮጵያ ላይ ከ1523 - 1659 ዓ.ም ድረስ ለ36 ዓመታት ነግሠዋል። ይህ የ36 ዓመት የአስተዳደር ዘመናቸው በእኔ ጥናት፣ መረዳትና ግንዛቤ መሠረት ከጎንደር 18 ነገሥታት /ምንም እንኳን የጎንደርን መንግሥት ነጋሢዎች ከሚናስ ጀምረው የሚቆጥሩ ድርሳናት ያሉ ቢሆንም፤ ከዐጤ ሠርፀ ድንግል እስከ ፈጻሜ መንግሥት ተክለ ጊዮርጊስ ድረስ/ ሁሉ ረጅሙ ነው። ንጉሡ በመንግሥታዊ አስተዳደር ዘመናቸው በአባታቸው ምክንያት የተፈጠረውን የሃይማኖት ብጥብጥ እንዲሰክን አድርገዋል። መናገሻቸው በሆነችው ጎንደር ሰባት አብያተ ክርስቲያናትን አሳንጸዋል። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ የሚያስመሰግኑ መንፈሳዊ ተግባራትንም በመከወን ሲኖሩ ቆይተው በወርሐ ጥቅምት ዕለተ ማክሰኞ ከረፋዱ ዐራት ሠዓት ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። መንበረ ሥልጣናቸውንም የለቀቁት በዚሁ እረፍታቸው ምክንያት ነው። ዐጤው ሲሞቱ የጎንደር ሕዝብ ብዛት 27 ሺህ ደርሶ እንደነበር ይነገራል።


መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፋሲል ካሳነጹዋቸው ሰባት አብያተ ክርስቲያናት መሐከል /ከፊት አቦ፣ ከፊት ሚካኤል፣ ከአደባባይ ኢየሱስ፣ ከእልፍኝ ጊዮርጊስ፣ ከመንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም እና ከአቡን ቤት ቅዱስ ገብርኤል/ አንዷ ነች።

ዐጤ ፋሲል ደብሯን ከተከሉ በኋላ መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ቅድስት ማርያም ተብላ እንድትጠራ ራሳቸው ስያሜውን አውጥተውላታል። ይህን ስያሜ ሊያወጡላት የቻሉት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን ማሳነጽ ከመጀመራቸው በፊት ለግንባታ ከመረጡት ወንበር በር በኩል በእንቁላል ግንብ ወደቤተ መንግሥቱ በሚወስደው አቅጣጫ ላይ የንጉሡ ግምጃ ቤት ነበር። በዚህ የተነሳ መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት የሚለውን ስም አገኘች። ዐጤው ቤተ ክርስቲያኗን ለመሥራት የፈለጉት ቤተ መንግሥታቸውን መሥራት በጀመሩበት ወቅት ካቡ እየፈረሰ ስለተቸገሩ የበቁ አባቶችን ያማክራሉ። ምክር የተጠየቁት አባቶችም የኢየሱስን እና የቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ቢሠሩ ቤተ መንግሥታቸው እንደሚጸና ስለተነገራቸው እንደሆነ በአባቶች ዘንድ ይነገራል።

ንጉሡ ቤተ ክርስቲያኒቱን እንዲያገለግሉ አምስት ልዑካን መድበውላት ነበር። በዐጤ ኢያሱ ጊዜ ግን እንደማንኛውም ደብር ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ቄስ፣ ዲያቆን፣ ገበዝና ዐቃቢ፣ ለዕቃ ቤቱ ጠባቂ ድመት፤ ለመረዋ ቤቱ ደወል፤ ለቅኔ ማኅሌቱ አለቃ፣ መሪጌታ ቀኝ

ጌታ፣ ግራ ጌታና ደብተራ ወ.ዘ.ተ. ተመድቦላት በ199 አገልጋዮች ትገለገል ነበር። በዐጤ ኢያሱ ዘመነ መንግሥት ደግሞ 150 ሊቃውንት ተመድበውላት ስትገለገል ቆይታለች።

ለመጀመሪያ ጊዜ የዐራቱ ጉባኤያት ማለትም የመጽሐፍተ ብሉያት፣ የመጽሐፍተ ሐዲሳት፣ የመጽሐፍተ መነኮሳትና የመጽሐፍተ ሊቃውንት ትምህርት የተጀመረው በመካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም እንደሆነ ይነገራል። ጉባኤ ቤቱ ብዙ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን አፍርቷል። አሁን ግን መጽሐፈ ሐዲሳት ብቻ እየተሰጠበት ይገኛል።



ፎቶ. መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ከተካይዋ ከዐጤ ፋሲል ጀምሮ በተለያዩ ነገሥታት መቀደሻ እና ማስቀደሻ እየተገበረላት ዘውዳዊው አገዛዝ እስካከተመበት 1960 አጋማሽ ድረስ ስትገለገል ቆይታለች። አሁን ግን ሕዝበ ክርስቲያኑ በሚሰጠው ገንዘብ ብቻ ነው የምትተዳደረው። መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያምን የሚያስተዳድሩት አስተዳዳሪዎች ሊቀ ማእምራን የሚል ስመ ማዕረግ እንዲኖራቸው በዐጤ ኢያሱ ተደንግጓል።

መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም በ1881 ዓ.ም በድርቡሾች ከፍተኛ የእሳት ውድመት ደርሶባታል። ወራሪው ኃይል ጎንደር ገብቶ የጥፋት እጁን ሲዘረጋ ቤተ ክርስቲያኒቷ በውስጧ ከሚገኙ ንዋያተ ቅዱሳት ጋር በተለኮሰባት እሳት ወድማለች። ካህናቱ ቀደም ብለው ታቦተ ሕጉን ከመንበሩ አውጥተው በጫካ ውስጥ ደብቀውት ስለነበር ከቃጠሎው ተርፏል። ታቦተ ሕጉ ጠላት እስከወጣበት ድረስ በሣር ሰቀላ ውስጥ በጊዜያዊነት ቆይቷል።

ከታቦተ ሕጉ በተጨማሪም ከቃጠሎ የተረፈች ሌላም ተዓምረኛ ሥዕል አለች። ይህች ሥዕል ከቃጠሎው የተረፈችው ሰዎች አሸሽተዋት ሳይሆን በእግዚአብሔር ተዓምር ነው። ሥዕሊቷን ቀዳማዊ የጤ ዮሐንስ እንባቸውን በማፍሰስና ቀለም በማስበጥበጥ ያሳሏት የቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕል ነች። ቤተ ክርስቲያኑ በእሳት ሲጋይ ያለማንም አጋዥነት ወጥታ ከፋሲል ግንብ አጥር ግቢ በጥሻ ውስጥ ተሰውራ ቆይታለች። ደርቦሾች ከአገር ወጥተው አገር መረጋጋት ሲጀምርና ታቦተ ሕጉ በጊዜያዊነት ከነበረበት የሰቀላ ቤት ወጥቶ ወደቀደመ ቦታው ሲመለስ ሥዕሊቷ በቅጥሩ ውስጥ በሚገኘው ዛፍ ሥር ተቀምጣ ተገኘች። ሥዕሊቷ ዛሬም ድረስ በቤተ መቅደሱ ውስጥ ትገኛለች።

አባቶች ቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ በመውደሙ የተነሳ ታቦተ ሕጉን ያሳረፉት በሣር ጊዜያዊ ሰቀላ በመሥራት ነበር። ነገር ግን ታቦተ ሕጉን በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ከ1936 — 1939 ዓ.ም ቅድስትና ቤተ መቅደስ ያለው አዲስ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቶለት ከብሯል። እቴጌ መነን አስፋውም ሰባት ሺህ በር በመበጀት ቅኔ ማኅሌት አሠርተዋል። ቤተ ክርስቲያኑ በድንጋይና በጭቃ ብቻ ስለነበር የተሠራው በ1985 ዓ.ም በወቅቱ የነበረው ሰበካ ጉባኤ ሕዝበ ክርስቲያኑን በማስተባበር ግድግዳውን ወለሉን በሲሚንቶ አሠርተውታል። በ1987 ዓ.ም ደግሞ መስኮቱን በመስታወትና በፍርግርግ ተሠርቷል።

መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ከተተከለችበት ዘመን አንስቶ በርካታ መመህራን በመምህርነት ሲያገለግሉ ቆይተዋል። ከሁሉም ግን ስማቸው በጉላት የሚነሳውና ታሪካቸው የሚነገረው መምህር ወልደ ሚካኤል ናቸው።

መምህር ወልደ ሚካኤል

- መምህር ወልደ ሚካኤል በመንፈስ አባታቸው በመመህር ወልደ አብ[125] ስም ነው የሚጠሩት። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሐዲሳት ትርጓሜ ተግባር የሚጀምረው ከሠርዌ ክርስቶስ ነው። መምህር ወልደ ሚካኤል ከሊቁ ሠርዌ ክርስቶስ ጀምሮ ሊቆጠሩ ዘጠነኛ መምህር ናቸው። መምህራኑም በቅደም ተከተል ሠርዌ ክርስቶስ፣ ጽጌ ድንግል፣ አባ ያዕቆብ፣ በትረ ክርስቶስ፣ አለቃ ጓንሁል፣ መምህር ኤስድሮስ፣ መምህር ሥነ ክርስቶስ፣ መምህር ወልደ አብ፣ መምህር ወልደ ሚካኤል ናቸው።

[125] የሸዋ ሰው ናቸው

መምህር ወልደ ሚካኤል እጅግ በርካታ መጽሐፍትን ያነበቡ የመረመሩና የተመራመሩ ዐራት ዓይና የተባሉ ሊቅ ነበሩ። በመካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ወንበር ዘርግተው በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል። ከደቀ መዛሙርቶቻቸው መሐከል ለአብነት መምህር ገብረ ማርያም፣ መምህር ወልደ ሩፋኤል፣ መምህር ወልደ አማኑኤል፣ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ፣ መምህር ተክለ ማርያም፣ መምህር ወልደ ሚካኤል፣ አለቃ ጎሩይ፣ አለቃ መንክር፣ መምህር እንግዳየሁ፣ መምህር ዘዮሐንስ[126] ይጠቀሳሉ። እኒህ አባት በደርቡሽ የወረራ ዘመን ስለሃይማኖታቸው ሲሉ ከስምንት ደቀ መዛሙርቶቻቸው ጋር ሰማዕትነትን ተቀብለዋል።

ደርቦሾች በ1881 ዓ.ም ጎንደርን ሁለት ጊዜ የወረሩ ሲሆን የጥፋት ተግባራቸውን ሲጀምሩ መምህር ወልደ ሚካኤል በመካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ወንበር ዘርግተው በማስተማር ላይ ነበሩ። የወራሪውን ጥፋት የተመለከቱ ወገኖች ወደእሳቸው መጥተው ከአካባቢው እንዲርቁና ነፍሳቸውን እንዲያከርሙ ይነግሯቸዋል። መምህር ግን እኔ ወዴትም አልሐድም ብለው ይጸናሉ። ደቀ መዛሙርቶቻቸውን ግን "ልጆቼ ሥጋችሁን የወደዳችሁ እንደሆነ ሽሹ ነፍሳችሁን የወደዳችሁ እንደሆነ ከኔ ጋር ሁኑ" ብለው ሀሳብ አቀረቡላቸው። ደቀ መዛሙርቱ አንድ ልብ ሆነው ከእሳቸው ጋር እንደሚሆኑ ገለጹላቸውና እዚያው ቀዩ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳሉ ድርቦሾች ወደቤተ ክርስቲያኑ ቅጽረ ግቢ ዘለቁ። እናም ሰይፍ መዘው ሃይማኖታችሁን ለውጡ አሏቸው። መምህር ወልደ ሚካኤል ግን ወንጌላቸውን ይዘው "ነዓአምን በአሐዱ አምላክ ሃይማኖቴን አልለውጥም" አሉ። ደቀ መዛሙርቱም እንደመመህራቸው በሃይማኖታቸው ጸኑ። ይህን የተመለከተው ወራሪ ኃይል ሰይፉን መዞ የመምህር ወልደ ሚካኤልን አንገት ከስምንት ደቀ መዛሙርታቸው ጋር ቀላቸው።

መምህር ወልደ ሚካኤልና እንደበግ የታረዱት ደቀ መዛርት በወቅቱ ቀባሪ አላገኙም ነበር። ምክንያቱም በስተግዋ አንድም ሰው አልነበረም። ግማሹ ሕዝብ ስለሃይማኖቱና ስለአገሩ ክብር ሲዋጋ ሞቷል። ግማሹም ሕይወቱን ለማክረም ሽሽቶ ከአካባቢው ርቋል። ነግር ግን የሰማዕታቱ አስከሬን አሞራም ሆነ ሌላ አውሬ ሳይበላው ሕዝቡ ወደከተማዋ እስኪመለስ ድረስ በወደቀበት ቦታ ቆይቷል።

የሚገርመውና እንደተዓምር የሚነገረው ይህ ብቻ ሳይሆን አስከሬኑ መጥፎ ሽታ ከማውጣት ይልቅ እንደሽቶ ያማረ መዓዛ ያወጣ ነበር። በኋላ ቀባሪዎችን ወደቦታው

[126] ዜና መዋዕል ዘብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ። አዲስ አበባ፣ ኅሐሴ 1978 ዓ.ም ገጽ 23

እንዲመጡ ያደረጋቸውም ይኸው መልካም መዓዛ ነበር። መዓዛው የጠራቸው ቀባሪዎች በቦታው ሲደርሱ የሁሉንም አስከሬን በክብር ያገኙት ሲሆን አንስተው ዛሬ በቤተ ክርስቲያኒቷ በላይኛው በር በኩል ይገኛል። ለእነዚህ ሰማዕታት መታሰቢያ የሚሆን የሰብከተ ወንጌል አዳራሽ መምህር ወልደ ሚካኤል ወልደ አብ በሚል ስያሜ በቅጽረ ግቢው ይገኛል። በቅጽረ ግቢው ቀድሞ የዐጤ ቴዎድሮስ አማካሪ እንደነበር የሚነገርለትና እንግሊዛዊ ዜግነት ያለው ፕላውዴን የተባለው ሰው አስከሬን አርፎበታል። በተጨማሪም በደርቡሽ አማካይነት የፈረሰው ቤተ ክርስቲያን መካነ ፍራሽ ታሪክን እየዘከረ እስከዛሬ ድረስ በግቢው ይገኛል።

<u>ምንጭ</u>

- በመካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ሰንበት ት/ቤ
  ተማሪዎች። መካነ ነገሥት ግምጃ ቤት ማርያም ቤተ
  ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ። ጎንደር 16 1995 /ኮፒ/
- አለማየሁ አንበሴ። <u>አዲስ አድማስ</u> ጋዜጣ። ህብረተሰብ። አድማስ አድቨርታይዚንግ
  ኃ.የተ.የግ.ማ.፣ ብርሃንና ሰላም ድርጅት። ሐምሌ 19 - 2006 ዓ.ም ገጽ 8
- ቶማስ በየነ። ‹‹የታሪክ ግምጃዋ ግምጃ ቤት ማርያም።›› የቴሌቪዥን መርሐ ግብር ማኅበረ
  ቅዱሳን፣ ኢቢኤስ ቴሌቪዥን። ታኅሣሥ 20- 2006 ዓ.ም።
- <u>ዜና መዋዕል ዘብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት
  ዘኢትዮጵያ</u>። አዲስ አበባ፣ ነሐሴ 1978 ዓ.ም ገጽ 22-23

30.<u>ዐርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን</u>

ዐርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን በጎንደር ከተማ የሚገኝ ነው። ቤተ ክርስቲያኑን የተከሉት አቤቶ አርምሐ ናቸው። የተተከለበት ዘመን 1666 ዓ.ም ነበር። አቤቶ አርምሐ ቀደም ተብሎ ታሪካቸው በዚህ ምዕራፍ የተነገረላቸው ጻድቁ የሚባሉት የዐጤ ዮሐንስ አንደኛ ልጅ ናቸው።

አንዳንድ ምንጮች እንደሚጠቁሙት ዐርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን የጎንደር ከተማ ከመመሥረቷ ከ1628 ዓ.ም በፊት እንደተተከለና ከከተማዋ መመሥረት በፊት ከተተከሉት ዐራት አብያተ ክርስቲያናት መሐከል አንዱ ነው።[127]

ልዑሉ መንበረ መንግሥቱን አልያዙም። ነገር ግን በዐርባዕቱ እንስሳ ስም ቤተ ክርስቲያን ለማሳነጽ በቅተዋል። ለቤተ ክርስቲያኑም የሚሆኑ 14 አገልጋዮችን መድበዋል። ለመተዳደሪያም በፎገራ ርስት ሰጥተዋል። ለቦታው መጠሪያ የሚሆን ልዩ ስም አልተሰጠውም።

ይህ ቤተ ክርስቲያን ደርቡሽ መጋቢት ሁለት ቀን ዐጤ ዮሐንስ ዐራተኛን ገድሎ ለሁለተኛ ጊዜ ጎንደርን በወረረ ወቅት በ1881 ዓ.ም ተቃጥሏል። ታቦቱ ግን በደባልነት አልፍኝ ጊዮርጊስ ተወስዶ ተቀምጦ ቆይቷል። በ1992 ዓ.ም በገበሬው ሕዝበ ክርስቲያን እንዲሠራ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንቅስቃሴ ተጀመረ። በቀድሞው የቤተ ክርስቲያኑ ፍራሽ ላይ /ልዑሉ ባሠሩትና ደርቡሽ ባቃጠለው/ መቃረቢያ ተሠርቶለት ሲገለገል ቆየ። ቅዳሴ ቤቱ በተከበረበት በዚህ ዕለት ጸበል ፈልቆ ታላቅ ፈውስ ሰጥቷል። እየሰጠም ይገኛል።

<u>ምንጭ</u>

- <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u>። ገጽ 264፣ 265
- <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ</u>። ገጽ 157- 164
- <u>አዲስ አድማስ</u> ጋዜጣ። ገጽ 19

31. <u>አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን</u>

ደብረ ገነት አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በጎንደር ከተማ ውስጥ ያለ ቀደምት ቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው በ1711 ዓ.ም ነው። ያሠሩት ደግሞ ዐጤ ዳዊት ሣልሳዊ ናቸው። የትክል ዘመኑን በተመለከተ አንዳንድ ድርሳናት ንጉሡ በነገሡ በአንደኛው ዓመት 1709 ዓ.ም እንደሆነ ይተርካሉ። ሌሎቹ ደግሞ በ1712 ዓ.ም ተተከለ ይላሉ።

---

[127] አለማየሁ አንበሴ። <u>አዲስ አድማስ</u> ጋዜጣ። ህብረተሰብ። አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.፣ ብርሃንና ሰላም ድርጅት። ሐምሌ 19 - 2006 ዓ.ም ገጽ 19

ሣልሳዊ ዐጤ ዳዊት

❖ ሣልሳዊ ዳዊት የመንግሥትን ዙፋን የያዙት ከዐጤ ዮስጦስ /ፀሐይ ሰገደ/ ቀጥሎ ነው፤ ዘመኑ ደግሞ 1708 ዓ.ም። ንጉሡ በዚህ ዘመን ሲነግሡ ዕድሜያቸው ሃያ አንድ ዓመት ነበር። ስም መንግሥታቸው አድባር ሰገድ የተሰኘ ሲሆን ሥርዓተ ንግሥ የፈጸሙላቸው በወቅቱ በመንበረ ፕትርክናው ላይ የነበሩት ግብፃዊው ጳጳስ አቡነ ማርቆስ ናቸው። ዕጨጌ ዘአማኑኤልም በንግሥናቸው ላይ ተገኝተዋል። እሳቸው ሲነግሡ ንጉሥ ዐጤ ዮስጦስ በሕይወት ነበሩ። ከነገሡ በኋላ ግን በዘጠንኛው ቀን ሞተዋል።

ሣልሳዊ ዐጤ ዳዊት በነገሡ ጊዜ በወቅቱ የነበሩት የአዘዞ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አባቶች በተለይም አባ መዝሙረ የተባሉት አባት "ጉዳይ አለንና ጉባኤ ይጠራልን" ይሏቸዋል። ንጉሡም ካህናቱን ሰብስበው ጉባኤው እንዲካሔድ ይሁንታ በመስጠት ጥሪ ተደረገ። በጉባኤው የቀረበው ጉዳይም በአባ መዝሙረ አንደበት የተሰማ ሲሆን ጉዳዩም ከባሕር ማዶ የመጡ ቄሶች በዐጤ ዮስጦስ ጊዜ በወልቃይት አይነ እግዚእ በተባለ ቦታ ተቀምጠዋል፤ ይጠሩና ሃይማኖታቸው ይጠየቅልን የሚል ነው።

ካህናቱ እንዳሉት ንጉሡ ፈረንጆቹን አስጠሯቸውና ጠየቋቸው። ሰዎቹ ሁለት የሮማ እና አንድ የነምሳ ዜጎች ሲሆኑ ያስመጧቸው ዐጤ ዮስጦስ ነበሩ። ምክንያቱ ደግሞ ንጉሡ በእነሱ አማካይነት የጦር መሳሪያና የተለያዩ ዕቃዎችን ከውጪ አገር ለማግኘት ያላቸው ፍላጎት ነበር። የሰዎቹ ስም ሣሙኤል፣ ዳዊትና ሚካኤል የሚባል ሲሆን በሃይማኖታቸው ካቶሊክ ነበሩ። በተደረገው ጉባኤ መሠረት በዐጤ ሱስንዮስ ዘመን የነበረውን የሃይማኖት ብጥብጥ እንዳያስነሱ በሚል ስጋት በአለቃ ክፍሌ ፍርድና በንጉሡ አፅዳቂነት እንዲገደሉ ሆኗል።
ንጉሥ ሣልሳዊ ዳዊት ከ1708 - 1713 ዓ.ም ለአምስት ዓመታት ያህል በመንበረ መንግሥቱ ተቀምጠው ሲያስተዳድሩ ቆይተው በግንቦት ወር አርፈዋል። በአልጋቸውም ወንድማቸው ዐጤ በካፋ ተቀምጠዋል።

ንጉሡ አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን የሠሩት በኖራ ግንብ ነው። የዐራት ማዕዘን ቅርፅም አለው። በየማዕዘናቱ ላይ የደወል ቤት ዓይነት ተሠርቶም ለመነኮሳት መጠለያ ሆኖ ያገለግል ነበር። አሁን ያለው አንዱ ብቻ ሲሆን ሦስቱ ፈርሰዋል። ቀድሞ መቅደስና ቅድስት ያለው ሲሆን ከ1960 ዎቹ ወዲህ የታቦት መዛሪያ የነበረው ዓውደ ምሕረቱ ወደ ቅኔ

ማህሌትነት ተቀይሯል። ቤተ ክርስቲያኑ ሙሉ በሙሉ በድንጋይ ግንብ የተሠራ ሲሆን ግቢው በዕድሜ ጠገብ ዛፎች የተሞላ ነው።



ፎቶ. አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን

ንጉሡ ቤተ ክርስቲያኑን ሠርተው ካጠናቀቁ በኋላ ሁለት መቶ ስልሳ ስድስት ደብተሮችን ለአገልጋይነት መድበዋል። መተዳደሪያ የሚሆንም ርስት በደምቢያ ሰጥተዋል። ለአስተዳዳሪው "መልአከ ገነት" የሚል ስመ ማዕረግ ተሰጥቶታል። አሁን ያለው ቤተ ክርስቲያን የግድግዳው የውስጠኛ ክፍል በልዩ ልዩ ሥዕላት የተጌጠ ነው። ሥዕሉን ያሠሩት መልአከ ገነት አካል በየነ ናቸው። መልአከ ገነት አካል የተቃጠለውን ቤተ ክርስቲያን ለማሳደስ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ያመለከቱና ያሠሩ ሰው ናቸው። የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ሆነውም ሲያገለግሉ ኖረዋል።

ዐጤ ቴዎድሮስ ከጎንደር ወደ ደቡብ ጎንደር /ምናልባትም ደብረ ታቦር ከተማ/ ቅርሶቹን ሲያስወስዱ የዚህ ቤተ ክርስቲያን ንብረት የሆነ "መጽሐፈ ሐዊ" የተባለ ትልቅ መጽሐፍና የአለቃው ልብስ ተወስዷል። መጽሐፉ በአሀያ የሚጫን መጽሐፍ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የአጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በስሩ የአቋቋም የአብነት ትምህርት ቤት አለ። ታቦቱ ተዓምራዊ መሆኑ ይነገርለታል። በ1990ዎቹ መግባደጃ ላይ አንድ ሌባ ቤተ መቅደስ ገብቶ የመቅደሱን መጋረጃ ሰርቆ ይሄዳል። በመንገድ ላይ እየሔደ ሳለ ዓይኑ ይከለላል። ከሚሔድበት የደብረ ብርሃን ሥላሴ አቅጣጫ ወደ አጣጣሚ ሚካኤል ሲዞር ዓይኑ ይበራለታል። በዚህ መዋተት ውስጥ ሆኖ ሌሊቱን ያነጋል። ሰምችም ያዩታል። የሆነውን

ሲጠይቁትም ሌባ መሆኑንና የተከሰተውን ተዓምር ይናገራል። በመጨረሻም ንብረቱን መልሶ አስረክቧል።

በአጣጣሚ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ከተቀበሩት ታላላቅ ሰዎች መሐከል አንዱ በሰባ ዓመት ዕድሜያቸው ለዙፋን የበቁት ዐጤ ዮሐንስ ሁለተኛ ናቸው። ዐጤ ዮሐንስ አንድ እጃቸው ቆራጣ በመሆኑ አንድ እጁ ዮሐንስ በመባልም ይታወቃሉ። የነገሡት ለአንድ ዓመት ብቻ ከ1761-1762 ዓ.ም ነው። እኚህ ንጉሥ ከአንድ ዓመት የግዛት ቆይታ በኋላ ሞተዋል።

በደርቡሽ ወረራ የጥፋት ስለባ ከሆኑት የጎንደር ከተማ አብያተ ክርስቲያናት መሐከል አንዱ ዛሬ በመሐል ጎንደር ከዐጤ ፋሲል ቤተ መንግሥት አቅራቢያ የሚገኘው አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ነው።

<u>ምንጭ</u>

- <u>የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ።</u> ዝኒ ከማሁ 223-231
- <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u> ዝኒ ከማሁ ገጽ 331፣ 332
- <u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ።</u> ዝኒ ከማሁ ገጽ 63
- የመጽሐፉ አዘጋጅ የካቲት 14/ 2004 ዓ.ም ያደረገው ቅኝት።

32. <u>ደፈጫ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን</u>

ደፈጫ ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያን መገኛዋ በጎንደር ነው። ቤተ ክርስቲያኗ የተሠራችው ከ1713-1723 ዓመታት ውስጥ በመንበረ መንግሥቱ ተቀምጠው አገሪቷን ሲያስተዳድሩ በነበሩት ንጉሥ ነው፤ በዐጤ በካፋ።

ዐጤ በካፋ መሲህ ሰገድ

- ዐጤ በካፋ መንበረ መንግሥቱን የያዙት ከሣልሳዊ ዳዊት /አድባር ሰገድ/ ቀጥለው ነው። በካፋ ዐጤ ዳዊት በነገሡበት ጊዜ አምልጠው ሔደው ነበር። ነገር ግን ንጉሡ ለአልጋቸው እንደሚያሰጓቸው በማመን አስይዘው በማስመጣት በወህኒ አምባ አሳስረዋቸው ቆይተዋል። ዐጤ ዳዊት ሦስተኛና በካፋ ወንድማማቾች መሆናቸውን ልብ ይሏል። ስማነታቸው ወይም ዝምድናቸው በአባት በኩል ነው። ዐጤ ዳዊት

የተወለዱት ከአድያም ሰገድ የሕግ ሚስት ከእቴጌ መለኮታዊት ነው፤ ዐጤ በካፋ ደግሞ ከንጉሥ እቁባት ከወ/ሮ ማርያማዊት።

አድያም ሰገድ ዐጤ ኢያሱ ወደ ምድረ ፃማ ይሔዳሉ። ምድረ ፃማ የወ/ሮ ማርያማዊት ርስት ነበር። ማርያማዊት እጅግ ሲበዛ ጸሎተኛ የሆኑና በመንፈሳዊነታቸው የታወቁ ሴት ነበሩ። ከዐጤው ጋር የሥጋ ግብር እስከፈፀሙበት ጊዜ ድረስ በድንግልና ቆይተዋል።

ከንጉሥ ጋር ባደረጉት የአንድ ቀን ግንኙነት ዐጤ በካፋን ጸንሰዋል። በካፋ በተወለዱ ጊዜ በፍቅርና በእንክብካቤ አሳድገዋቸዋል። ንጉሡም መንግሥታቸውን ወርሰው አገሩን በሰላም እንደሚያስተዳድሩ ተናግረው ነበር። በንግራቸው መሠረትም ከዐራት ነገሥታት ማለትም ከወንድማቸው ከዐጤ ተክለ ሃይማኖት ከአጎታቸው ከዐጤ ቴዎፍሎስ፣ ከዐጤ ዮስጦስ፣ ከዐጤ ዳዊት ቀጥሎ መንበረ ዙፋኑን ይዘው ከዘጠኝ ዓመት በላይ ሕዝቡን አስተዳድረዋል። በካፋ ገና የዐሥር ዓመት ልዑል ከነበሩበት ዕድሜ ጀምሮ ከአባታቸው ጋር ለአደን ይወጡ ነበር። በአደኑ ጉዞ ላይም ያገኟቸው ባሕታዊያን ሁሉ እንደሚነግሡ ተንብየውላቸዋል።

በካፋ በወህኒ አምባ እስር ላይ ባሉበት ወቅት ጊዜያቸውን ያሳልፉ የነበሩት በጸምና በጸሎት ነው። በቀን የሚመገቡትም አንድ ጊዜ ሲሆን እሱም በዘጠኝ ሠዓት ነው። በካፋ ዘውድ ሲጫኑ "መሲህ ሰገድ" የሚል ስመ መንግሥት ተሰጥቷቸዋል። ከነገሡ በኋላ በሥርዓተ ተክሊል ከእቴጌ አዋልደ ንግሥት ጋር ጋብቻ ጥቅምት 29 ቀን ፈጽመዋል። ይህ ጋብቻ ለአንድ ቀን ብቻ የቆየ ነው። በዚህ ዕድሜውም በመጽሐፉ አዘጋጅ መረዳት በኢትዮጵያ ከነገሡ ነገሥታት አጭር የጋብቻ ዕድሜ ያለው ብቸኛ ጋብቻ ነው። ጋብቻው የተፈጸመው በሞት ነው።

ሥርዓተ ተክሊል ከፈጸሙበት ቤተ ክርስቲያን የመጡት ንጉሡና ንግሥቲቱ እስከ እኩለ ሌሊት ግብር ሲያበሉ ቆይተው በቀሪው ሌሊት ለሕልፈተ ሕይወት በቅተዋል። ምክንያቱ ምን እንደሆነ አይታወቅም። ይህ ጋብቻ የተፈጸመው በ1715 ወይም 1716 ዓ.ም እንደሆነ መገመት ይቻላል። ምክንያቱም ጋብቻው የተፈጸመው ንጉሡ ጃዊሶችን /ሸፍተውባቸው ነበር/ ድል ካደረጓቸው በኋላ ነው። ይህ ሽፍትነት የተነሳውና ድሉ የተገኘው በ1715 ዓ.ም መሆኑ በታሪክ ድርሳናት ላይ ተመዝግቦ ይገኛል።

ንጉሡ ዐጤ በካፋ የመጀመሪያው ጋብቻቸው በአንድ ቀን ከተፈጸመ በኋላ ነው ከታላቋ ንግሥት እቴጌ ምንትዋብ ጋር የተጋቡት። የንግሥቲቱ የዘር ሐረግ ከአቤቶ ፊቅጦር የዘር ሐረግ ይመዘዛል። አቤቶ ፊቅጦር የዐጤ ልብነ ድንግል የመጀመሪያ ልጅ ሲሆኑ "ፊቅጦር" ይሞታል በሚለው ትንቢት መሠረት ሞተዋል። የሞቱትም ከኢማም አሕመድ ጋር ደዋሮ ላይ በተደረገው ጦርነት ሚያዚያ 12 ቀን ነው። ንጉሡ በካፋ ከዚህ ጋብቻቸው "ብርሃን ሰገድ" በሚል ስመ መንግሥት የነገሡትንና የመጀመሪያ ልጃቸውን ዳግማዊ ኢያሱን ወልደዋል።

እቴጌ ምንትዋብ የዐጤ በካፋ ሚስት ለመሆን የበቃችው በአጋጣሚ ሳይሆን በፈቃደ እግዚአብሔር እንደሆነ ይነገራል። የእቴጌይቱ እናት ወይዘሮ እንኮየ ምንትዋብን ነፍሰ ጡር ሆና እያለ ባለቤታ ይሞታል። በዚህም ሳቢያ ከቋራ ተሰድዳ መጥታ ያረፈችው ከመከም በተባለው ቦታ ነው።

ከመከም የእንኮየ የእናቷ አገር ነው። ቦታው ዛሬም ድረስ እንኮየ መሬት እየተባለ ይጠራል። ምንትዋብ እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት 80 ቀን ሲሞላት ክርስትና የተነሳችው በዚህ ቤተ ክርስቲያን ነው። ምንትዋብ ለአቅመ ሄዋን ስትደርስ[128] በወቅቱ በጣራ ገዳም የነበሩት አባት አባ ኤርሚያስ ወደ ቤተ መንግሥት ይዘሻት ሒጂ በዚያ የሚጠብቃት ትልቅ ዕድል አሳት ብለው ለወይዘሮ እንኮየ እግዚአብሔር የገለጠላቸውን በመንገራቸው እናትየዋ ወደ ጎንደር ቤተ መንግሥት ይዛት ሔዳለች። ምንትዋብ በዚህ መሠረት በካፋን አግብታ በሥልጣኑ ተደላድላለች።

ዐጤ በካፋ /መስቀሀ ..../ ጠላትና ወዳጄን እለይበታለሁ ብለው በዘየዱት መላ ታምሜያለሁ ብለው ከቤታቸው በተኙ ጊዜ የአሥር አለቃ አድርገውት የነበረው ብላቴን ጌታ ኮኾ ሌላ ንጉሥ ለማንገሥ ይሰናዳ ጀምሮ ነበር። በዚህ ጊዜ በአደባባይ ወጥተው ታዩ። ብላቴን ጌታም ያሰበውን ሳያደርግ ቀረ። ይህ የሆነው በ1722 ዓ.ም ነው። ከአንድ ዓመት በኋላ ግን በ1723 ዓ.ም ንጉሡ በጽኑ ታመመ። ሕመማቸውም ለሕልፈተ ሕይወት አብቅቷቸዋል።

---

128 - ምንትዋብ ለአቅመ አዳም ስትደርስ እንኮየ አንድ ፈተና ገጥሟት እንደነበር አባቶች ይናገራሉ። ከምከም መጥታ በተቀመጠች ጊዜ ቤተሰቦቿ አገልጋይ እንዲሆናት አንድ ባርያ ከይፋግ ገዝተው አምጥተው ሰጥተዋት ነበር። ይህ ባሪያ ምንትዋብ አድጋ ባያት ጊዜ ለእንኮየ ሦስት ጥያቄዎችን ያቀርባል። አንደኛው ልጅሽን ዳሪልኝ፤ ሁለተኛው ክርስትሽ አክፍይኝ፤ ሦስተኛው ይህን የማታደርጊልኝ ከሆነ ጥየሽ እሔዳለሁ የሚል ነበር። በዚህ ጊዜ እንኮየ ተጨንቃ በአቅራቢያዋ ወደነበሩ አዛውንት በመሔድ ከባሪያዋ የቀረበላትን ጥያቄ ትነግራቸዋለች። አዛውንቱ ለዚህ የሚሰጡት መልስ እንደሚቸግራቸው ነገር ግን ጣራ ገዳም በብሕትውና ወደሚኖሩት አባ ኤርሚያስ ዘንድ ብትሔድ መፍትሔ እንደምታገኝ ያስረዷታል። እሷም የአዛውንቱን ምክር ተቀብላ ወደ አባ ኤርሚያስ ዘንድ ትሔድና ታማክራቸዋለች። ባሕታዊውም ወደ ጎንደር ይዛት እንድትሔድ ምክር ይለግሷታል።

ዐጤው የደፈጫ ኪዳነ ምሕረትን ቤተ ክርስቲያን ሊሠሩ የቻሉበት የራሱ ታሪክ አለው። ታሪኩ እንዲህ ነው። በቅሎዎቻቸው ይጠበቁበት የነበረ አንድ ቦታ ነበረ። በአንድ ወቅት ከዚህ ቦታ ላይ ሌሊት አንደኛው በቅሎ ይጠፋል። በቅሎውንም ለመፈለግ ፍለጋ ሲወጡ በወቅቱ ሽንብራ ከተወቃበት ቦታ ላይ ደፈጫ እየበላ ያገኙታል። ደፈጫ ማለት የሽንብራ ገለባ ማለት ነው።

በቅሎውን ከጅብ መንጋጋ የታደገችላቸው ኪዳነ ምሕረት እንደሆነች ጠይቀው በመረዳታቸው በቦታው /ሽንብራው በተወቃበት አውድማ ላይ/ ቤተ ክርስቲያን ሠሩ። የኪዳነ ምሕረትንም ጽላት አስገብተው ቅዳሴ ቤቱን አከበሩ። "ደብረ ሕይወት" የሚል የክብር ስምም ሰጧት። አንድ መቶ ሃያ አገልጋይ ካህናትን መደቡላት። ለመተዳደሪያም 16 የጭቃ ርስት ሰጧት።

ቤተ ክርስቲያኗ የተሠራችው በሥንደር የአሠራር ስልት ነው። በኖራ ክብ ቅርፅ ያላት ሆኖ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስ ነበራት። ደርቡሽ ጎንደር በገባ ጊዜ በእሳት አያይዟታል። በዚህ ቃጠሎም የሣር ክፍክፍ ጣሪያዋ፣ የበርና የመስኮት እንጨቶቿ ጋይተዋል። ይህ ከሆነ በኋላ ታቦተ ሕጉ በዕቃ ቤት ገብቶ እስከ ኢጣሊያ ወረራ ድረስ ቆይታል። በዚህ ዘመን /በፋሽስት የወረራ ዘመን/ የዕቃ ቤቱ በኢጣሊያ ቆርቆሮ ተከድኗል።

ፋሽስት ኢጣሊያ አገራችንን ለቅቆ ከወጣ በኋላ ሰፋ ያለ መቃረቢያ ተሠርቶ አገልግሎቱ ቀጠለ። ነገር ግን ነሐሴ 1 ቀን 1969 ዓ.ም በድጋሚ ቃጠሎ ደርሶበታል። የእሳቱ መነሻ ምክንያት ግን ምን እንደሆነ አይታወቅም። በ1971-1972 ዓ.ም አዲስ የቆርቆሮ ቤተ ክርስቲያን ወ/ሮ ሩቅነሽ ዋሴ የተባሉ ክርስቲያን አሠርተውታል። በወቅቱ ስምንት ሺህ ብር የወጣበት ሲሆን፣ ቁመቱ 4 ሜትር ወርዱ 15 x 15 ሜትር ነበር። ንጉሡ ዐጤ በካፋ ያሠሩት ቤተ ክርስቲያን እስከዛሬ ድረስ ጣሪያ፣ በርና መስኮት ሳይኖረው ታሪክን እየነገረ ተቀርሶ ተቀምጧል።

ምንጭ

- የአማርኛ የቤተ ክርስቲያን መዝገበ ቃላት። ቅጽ 11 ገጽ 26
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከኢማም አሕመድ እስከ ዐጤ ቴዎድሮስ። ዝኒ ከማሁ ገጽ 54
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነ ድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ። ዝኒ ከማሁ። 232-255
- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ዝኒ ከማሁ። ገጽ 549-550
- እርቅይሁን በላይነህ። ‹‹ቅድስት ጣራ ገዳም›› የቱሊቪዥን መርሐ ግብር ጽሑፍ

33. ቅድስት ጣራ የአንደነት ገዳም

ቅድስት ጣራ የአንድነት ገዳም መገኛው በደቡብ ጎንደር አገረ ስብከት በሊቦ ከምከም ወረዳ ነው። የተመሠረተው በዐጤ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት /ከ1533 - 1551 ዓ.ም/ ነው። መሥራቹ ደግሞ አባ ገላውዴዎስ የተባሉ የጎጃም ሰው ናቸው። በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ጥቅጥቅ ያለ ደን አለ። ደኑ የተሰወሩ አባቶች እንዳሉበት ስለሚነገርለት አይቆረጥም። በሰውም አይጠበቅም፤ ጠባቂው ነብር ነው። ነብሩ በገዳሙ ያሉ አባቶች ተቀያይመው እንዲውሉና እንዲያድሩ አያደርግም።[129] የገዳማዊያኑን ከብቶችም ይጠብቃል እንጂ አይተናኮልም። በገዳሙ አካባቢ ከነብር በቀር የሥጋ በሊታዎቹ ጅቦችም ሆኑ ሣር ነጪታዎቹ ዝንጀሮዎች ድርሽ አይሉም፤ ግዝት በመሆኑ።

አባ ገላውዴዎስ

- አባ ገላውዴዎስ የት መጣነታቸው ጎጃም ዲማ አካባቢ ይናጫ አቦ ከተባለ ቦታ ነው። ገዳሙን ከመመሥረታቸው በፊት በአካባቢው ባለ ዋሻ ውስጥ ለ40 ዓመታት ያህል ዘግተው ቆይተዋል። ከዐርባ ዓመታት በኋላ ማለትም በዐርባ አንደኛው ዓመት ከዋሻው ወጥተው እንደ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀኖና መሠረት ለማዕትነት ወደ ተሰጣቸው ንጉሥ ዐጤ ገላውዴዎስ ዘንድ ይሔዱና በቦታው ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ማሰባቸውን ገልጸው መልካም ፈቃዳቸውን ይጠይቋቸዋል። ንጉሡም በጉዳዩ ተስማምተው በገዳሙ አካባቢ ያለውን መሬት ርስተ ጉልት አድርገው ይሰጧቸዋል።

---

[129] - ለዚህ ማሳያ የሚሆን አንድ የቅርብ ጊዜ ታሪክ አለ። በገዳሙ አሁን በማገልገል ላይ በሚገኙት ቁሰ ገበዝና መጋቢ መሐከል ጊዜያዊ ግጭት ይፈጠራል። የግጭቱ መነሻ በቁሰ ገበዙ አማካይነት መጋቢው ሳያውቁ ቅዳሴ ተከናውኖ ሲያበቃ አገልጋዮቹ ምግብ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ። አገልጋዮቹ የጠየቁትን ምግብ እንዲሰጣቸው ቁሰ ገበዙ ወደ መጋቢው ይልኳቸዋል። መጋቢው እኔ ሳላውቅ የተከናወነ በመሆኑ ያለፕሮግራሜ ልሰጥ አልችልም ይላሉ። በዚህ መሐከል ሁለቱም ግጭት ውስጥ ይገባሉ። ሲያስማሙ የመጡትንም አባቶች አሸንፈው በጸብ ይለያያሉ። ሌሊት ግን በገዳሙ ያሉት ነብራት ሥራቸውን ይጀምራሉ። አንደኛው ወደ መጋቢው በመሔድ አላስተኛ ይላቸዋል። በሌላ በኩል ያለው ነብር ደግሞ ቁሰ ገበዙ ወደ ቤተ መቅደስ ገብተው አግልግሎት ለመጀመር ሲሔዱ መንገድ ላይ ቆሞ እንዳያልፉ ይከለክላቸዋል። መከልከል ብቻ አልበቃውም ወደ መጋቢው ዘንድ እየነዳ ወስዶ ከበዓታቸው ያደርሳቸዋል። ለአግልግሎት የወጡት ሌሎች ካህናት ድምጽ ለምተው ሲሔዱ የተጣሉት ሰዎች ተፋጥጠው ያያሉ። ምን እንደተፈጠረ ሲጠይቋቸውም የሆነውን በዝርዝር ይናገራሉ። በመጨረሻም እንዲያስታርቋቸው በመጠየቃቸው በአባቶች ፊት ልባዊ ይቅርታ ይጠያየቃሉ። ከእርቅ በኋላ ለአገልግሎት ወደ ቤተ መቅደሱ ሲሔዱ ቁሰ ገበዙን ወደ መጋቢው በዓት የመለሰው ነብር በቀድሞው ቦታ ተቀምጦ ሲጠብቅ አዩት። ነብሩ የአባቶቹን እርቅ ልባዊ መሆኑን ሲያውቅ ተነስቶ ወደ ጫካው ለመግባት ችሏል።
/‹‹ቅድስት ጣራ ገዳም››። እርቅይሁን በላይነህ። የቴሌቪዥን መርሐ ግብር ጽሑፍ።/

አባ ገላውዴዎስ የመሠረቱትን ገዳም በዐሥራ ሁለት ግመሎች ከዋልድባ ገዳም አፈር እያስጫኑ ዙሪያውን ረጭተውታል።[130] ይህን ማድረጋቸው የገዳሙ ሥርዓት ልክ እንደ ዋልድባ እንዲሆን ሀሳብ ስለነበራቸው ነው። ገዳሙ ከተመሠረተ ጊዜ ጀምሮ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ 12 አባቶች በአበምኔትነት ተመርጠው አገልግለውታል። የመጀመሪያው አበምኔት ራሳቸው አባ ገላውዴዎስ ናቸው። ሁለተኛው ግን አባ ኤርሚያስ ናቸው።

አባ ኤርሚያስ

አባ ኤርሚያስ በቅድስት ጣራ ገዳም እጅግ ረጅሙን ዘመን በሕይወት ኖረው ሲያገለግሉ የቆዩ ልብ ብርሃን የሆኑ ዓይነ ሥውር አባት ናቸው። እንደ አፈ ታሪክ ትርክት ከሆነ 480 ዓመታትን በሕይወት ኖረዋል። ለገዳሙ መጠሪያ የሆነውን ‹‹ጣራ›› የሚል ስያሜ ያወጡለትም እሳቸው እንደሆኑ ይነገራል። ታሪኩ እንዲህ ነው። አባ ገላውዴዎስ ወደ አገረ ኢየሩሳሌም ሊሄዱ እንዳሰቡና ጸሎት እንዲያደርጉላቸው ሲነግሯቸው አባ ኤርሚያስ እጅጉን ያዝናሉ። ወዲያውም ከሰማይ የእግዚአብሔር መልአክ ሲጣራ ይሰማሉ። በዚህ ጊዜ ተጣራ ብለው ‹‹ጣራ›› የሚለውን ቃል የገዳሙ ስያሜ አደረጉት።

አባ ኤርሚያስ እረፍታቸው እጅግ አስገራሚና አሰደናቂ ታሪክ አለው። ከእነዚህ ዓመታት በኋላ እረፍታቸው በደረሰ ጊዜ ቤተ መቅደስ አገልግለው ሲወጡ እንቅፋት መትቷቸው ይወድቃሉ። ከወደቁበት ቦታ ሳይነሱ ጉንዳን ይሰፍርባቸዋል። መውደቃቸውን ተመልክተው የነበሩት ረድዓቸው የነበሩ ሦስት መነኮሳይያት መጥተው ሊያነሷቸው ይሞክራሉ። ነገር ግን ጻድቁ እግዚአብሔር ፊቅዶ እረፍታቸውን በጉንዳን ንክሻ ሊያደርገው እንደሆነ በማመን ተውኝ አታንሱኝ ይላሉ። መነኮሳይያቱም ማን አባት ይሆነናል ብለው በጠየቋቸው ጊዜ እናንተ ወደ እመ ምዑዝ እና ወለተ ጴጥሮስ እየተመላለሳችሁ ገዳሙን ታገለግላላችሁ ብለው ጸጋቸውን ሰጥተዋቸው አርፈዋል። ጻድቁ አባ ኤርሚያስ አጽማቸው በዚያው በገዳሙ አርፏል። መቃብራቸው በፍርስራሽ ካብ ታጥሮ ዛሬም ይታያል።

---

[130] የገዳሙ አባቶች እንደሚለጡት ትርክት ከሆነ ቤተ ክርስቲያኑን ለመሥራት የቻሉት ከእግዚአብሔር በተሠጣቸው ትዕዛዝ መሰረት ነው። ትዕዛዙ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው አፈር እንዲያመጡና ቤተ መቅደሱን እንዲያንጹ የሚያደርግ ነበር።

ምንም እንኳን ትክክለኛ ዘመኑ ባይታወቅም ይህ ገዳም በዚህ መልኩ የተገደመውና የቀናው በ16 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መንበረ መንግሥቱን ከአባታቸው ከዐጤ ልብነ ድንግል የተረከቡትና ለ18 ዓመታት በነገሡት ሰማዕቱ ንጉሥ በገላውዴዎስ ዘመን ነው። ይህም ማለት ከ1533- 1551 ዓ.ም ተመሥርቷል ማለት ነው።

በገዳሙ የቅድስት ድንግል ማርያም እና የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። የአቡነ አዎስጣቴዎስ ቤተ ክርስቲያን ለመጀመሪያ ጊዜ የተሠራው በአባ ገላዎዴዎስ እንደሆነ መዛግብት ያስረዳሉ።

የቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን በጣራ ገዳም


በገዳሙ የምትገኘውን የቅድስት ድንግል ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ያሠራችው እቴጌ ምንትዋብ ነች። እንደ አባቶች ትርክት ከሆነ እቴጌይቱ ቤተ ክርስቲያኗን የሠራችው ንግሥትነትን በተቀዳጀች በሁተኛው ዓመት ነው። ይህ ከሆነ ደግሞ የዐጤ በካፋ /የባለቤቷ/ የግዛት ዘመን ከ1713-1723 ዓ.ም በመሆኑ የትክል ዘመነ 1715 ዓ.ም ነው ማለት ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱን ትክል በተመለከተ ራሱን የቻለ አስገራሚ ታሪክ ያለው ሲሆን ይኸውም እቴጌይቱ ካየችው ራዕይ ጋር የተያያዘ ነው።

እቴጌ ምንትዋብ ከባለቤቷ ጎን ሆና ዙፋኑን ከያዘች በኋላ ለዚህ ዓይነቱ ክብር የበቃችው በገዳሙና በገዳሙ በነበሩት አባት በአባ ኤርሚያስ ትንቢትና ጸሎት አማካይነት ነው። በመሆኑም ወደ ቦታው እየተመላለሰች ሥጋ ወ ደሙ ትቀበል ነበር። በሁለተኛውም ዓመት የአቡነ ኤዎስጣቴዎስ ዓመታዊ ክብረ በዓል ስለነበር መስከረም 18 ቀን ወደ ገዳሙ ትመጣለች። እናም ድንኳን ደኩና ትቀመጣለች።

ሥጋ ወ ደሙ ተቀብላ በነበረችበት አንድ ለሊት ነጭ ንቦች ወዳለችበት ቦታ መጥተው ሲከቧትና ሳር ቅጠሉን ቀስመው ሲሔዱ ትመለከታለች። ጉዳዩ እጅግ ያስጨንቃትና ወደ አቡነ ኤርሚያስ ዘንድ ገብታ ያየችውን ራዕይ ትነግራቸዋለች። በመቀጠልም ጸጋ ልነጠቅ ነወይ ብላ ትጠይቃቸወዋለች። አባ ኤርሚያስም አይዞሽ ይህ ጸጋ በረከት ነው ንቦቹ ቀስመው የሔዱት ካህናቱ ሥጋ ወ ደሙን ሲያቀብሉሽ የነጠበውን ቀስመው በጫካው ላሉ ሥውራን አባቶች ሊሠጡ ነው ይሏታል።

እቴጌ ምንትዋብ የራዕዩን ትርጓሜ ከሰማች በኋላ ለባሕታዊው አንድ ጥያቄ ታቀርባለች። ጥያቄዋም በገዳሙ አንድ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ትችል እንደሆነ የሚማጸን ነበር። አባ ኤርሚያስም ለሰባት ቀናት /አንድ ሱባዔ/ ያህል እንድትታገሳቸውና እግዚአብሔርን ጠይቀው

መልሱን እንዲነግሯት ያሳስቧታል። እሷም አሺ ብላ ወደ መናገሻ ከተማዋ ትሔዳለች። ከሰባት ቀናት በኋላ አባ ኤርሚያስ ወደቤተ መንግሥቱ መልዕክተኛ ልከው ቤተ ክርስቲያኑን መሥራት እንደምትችል ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያኑ መሥሪያ የሚሆነው ገንዘብ ከሕዝብ የተውጣጣ ሳይሆን ከራሷና ከባሏ ብቻ የወጣ እንዲሆን ያሳስባሉ። እሷም አሺ ብላ ቤተ ክርስቲያኑን ማሠራት ትጀምራለች። ቤተ ክርሲያኑንም እጅግ ባማረ መልኩ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ሠርታ ታስረክባለች።



ፎቶ. ጣራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

እቴጌ ምንትዋብ በሠራችው ቤተ መቅደስ ውስጥ የገባችው የቅድስት ድንግል ማርያም ጽላት ነች። ይህ የሆነው በአጋጣሚ አይመስልም። እንዲያውም ቅድስት ድንግል ማርያም ከልጇ ጋር ተስድዳ ወደ አገራችን ገብታ በነበረበት ዘመን በጣና ቂርቆስ ቆይታ ከወጣች በኋላ በቀጥታ ወደ ጣራ ገዳም መጥታ ለ4 ወር ከ25 ቀን ተቀምጣለች የሚል ትርክት በመኖሩ ይመስላል። እቴጌይቱ ያሠራችው ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ በመልካም ሁኔታ ላይ ሆኖ ይታያል።

እንደገዳሙ አባቶች ትርክት ከሆነ ቤተ ክርስቲያኑ ምንም ዓይነት አደጋ እንዳልደረሰበት ይገልጻሉ። ነገር ግን በኢማም አሕመድ ዘመን ለቤተ መቅደሱ የተተከለው መድፍ ዕቃ ቤቱን መትቶት እንዳወደመው ይናገራሉ።

በእኔ እምነት ሁለቱም ዓይነት ትርክት ተዓማኒነት የላቸውም። ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው በዐጤ ገላውዴዎስ ዘመን ማለትም ከ1533-1551 ዓ.ም ነው። ኢማም

አሕመድ ተነስቶ የነበረው ደግሞ ከዚህ ዘመን በፊት ነው። እርግጥ ነው በዐጤው ዘመንም ነበር። ነገር ግን ሁኔታዎች እንደሚያመለክቱት ከሆነ ቤተ ክርስቲያኑ የተሠራው ንጉሡ አሕመድን ድል አድርገው በሥልጣናቸው ከተደላደሉ በኋላ ነው። ሁለተኛው ተዓማኒነት የሚጎድለው ትርክት ደግሞ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት በ1993 ዓ.ም እድሳት እስከተደረገለት ጊዜ ድረስ አልፈረሰም የሚለው ነው። የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ከሆነ ለሁለት ጊዜ ሰው ሰራሽ በሆነ ሁኔታ በእሳት ጋይቷል።



ፎቶ. የአቡነ ኤምስጣቴዎስ ቤተ ክርስቲያን

የመጀመሪያው በደርቡሽ የወረራ ዘመን የሆነ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በደርቡሽ የተቃጠለውን ቤተ ክርስቲያን የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን ከመነኮሳቱ ጋር ተረባርበው ካሠሩት በኋላ የተከሰተው ሲሆን የጥፋቱ አላወራዎች ፋሽስቶች ነበሩ። ለሁለተኛ ጊዜ በፋሽስቶች ሲቃጠል አገልግሎቱ በመቃረቢያ ውስጥ ሆኖ እንዲቀጥል ተደርጓል። የመቃረቢያው ግድግዳ የመፈራረስና ጣሪያውም የማፍሰስ አደጋ ተጋርጦበት እንደነበር <u>የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች</u> ይተርካል።

አሁን ያለው የአቡነ ኤምስጣቴዎስ ቤተ መቅደስ የታደሰው በ1993 ዓ.ም ነው። እድሳቱ ሰባት ዓመታትን ፈጅቶ ጥር ሁለት ቀን 1999 ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል። እንዲታደስ ያደረጉትም የቅዱስ ላሊበላ መንፈሳዊ የጉዞ ማኅበር አባላቶች ናቸው።

አቡነ ኤምስጣቴምስ

❖ ክርስቶስ ሞዓ /ዘክርስቶስ/ እና ሥነ ሕይወት እግዚ ክብራ ከተሰኙ ባልና ሚስት በቀደሞው አጠራር ትግራይ[131] እንደርታ አውራጃ በድርአይ ወረዳ በዳኔ ልዩ ስሙ ድርባ አቡነ ያስይ በተባለ ቀበሌ ሐምሌ 21 ቀን ሕጻን ተወለደ። ይህ ሕጻን የተወለደው በብሥራተ መልአክ ነው ሲሆን የያኔ ስሙ ማዕቀበ እግዚእ ነበር።

ማዕቀበ እግዚእ ገና በብላቴናነት ዘመኑ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመማር ችሏል። ዳዊት ደግሟል። ጎላም የእናቱ ወንድም ወደ ሆነው አባ ዘካርያስ ዘንድ ወደ ገርዓልታ ገዳም ሔዶ ተማረ። በመጨረሻም በዚሁ በአጎቱ እጅ መነኰሰ። ከዚህ በኋላ አቡነ ገብረ መስቀል ዘእንደርታ፣ አቡነ ሄኖክ ዘእንደርታ፣ አቡነ ጴዋ ወንጌል ዘእንደርታ፣ አቡነ ማቴምስ ዘእንደርታ፣ አቡነ መርቆርዮስ ዘእንደርታ፣ አቡነ ገብረ ኢየሱስ ዘእንደርታ የተባሉ ስድስት ታላላቅ አባቶች አስተምሮ አመንኩሷል። አብሯቸውም ኖሯል። ከእነዚህም ውጪ ሌሎች 47 አባቶችን አስተምሮ አመንኩሷል። ከ47ቱ መሐከል አቡነ አብሳዲ የተባሉት የማነ ብርሃን አንዱ ናቸው።

አባ ኤምስጣቴምስ ድቁናን ተቀብሎ ከእናቱ ጋር ጥቂት እንደቆየ ወደ ኤርትራ ሔደ። ሠራኤ በተባለች ቦታ የራሱን ገዳም መሥርቷል። ከዕለታት በአንዲቷ ቀን እግዚአብሔር ተገልጦለት መላዋን ኢትዮጵያን እየተዘዋወረ እንዲያስተምር አዘዘው። እንደታዘዘው አደረገ። ኢየሩሳሌምን ሁለት ጊዜ ተሳልሟል። አቡነ ኤምስጣቴምስ በመሠረተው ገዳም አባ አብሳዲን ሾሞ መጀመሪያ ካመነኰሳቸው አባቶች አባ ባኪሞስን፣ አባ መርቆርዮስንና አባ ገብረ ኢየሱስን በ1337 ዓ.ም አስከትሎ ምድረ ግብፅ ገባ።

ግብፅ የሔደበት ዐቢይ ጉዳይ በሰንበት በዓል አከባበር ላይ የተፈጠረው ክርክር ነበር። በዚህም የተነሣ ቅዳሜና እሁድ መከበር ያለባቸው ሰንበታት ናቸው ብሎ ደገፈ። በዚህም በወቅቱ ከገጠሪቱ ግብፃዊ ጳጳስና በደቡብ ኢትዮጵያ ከሚኖሩ አባቶች ጋር ሳይስማማ ቀረ። ከግብፅ ቀጥሎ ወደ አገረ ኢየሩሳሌም ተጓዘ። የኢየሩሳሌሙን ጉዞ በተመለከተ ሊቀ ብርሃናት መርቆርዮስ አረጋ <u>የቅዱሳን ታሪክ</u> በተሰኘ መጽሐፋቸው ገጽ 95 ላይ በዐጤ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት ከግብፅ ተሹመው የመጡትን አቡነ ያዕቆብን ለመቀበል ምጽዋ ሔዶ ከተቀበላቸው በኋላ ወደ ኤርትራ ገብቶ ነበር። ከዚህ

[131] - ኤርትራዊ የሚያደርጓቸው አሉ።

በኋላ በኤርትራ ባሉ መነኮሳት ተበሳጭቶ ወደ ኢየሩሳሌም ሔጄ ብቀመጥ እወዳለሁ ብሎ እንደተጓዘ ተርክዋል።



፶፮. አቡነ ኤዎስጣቴዎስ

በደብረ ከርም ዘእንደርታ 7 ዓመት፤ በአቦር ዘመርታ 7 ዓመት፤ በሸመና ዘእንደርታ 7 ዓመት፤ በማይቁርቁር በስሐቲ 10 ዓመት፤ በደብረ ብርበላ ዘእንባ ሰነይቲ 7 ዓመት፤ ኢየሩሳሌም ከመሔዱ በፊት በጎጃም 31 ዓመት፤ በአርመንያ 14 ዓመት ተቀምጧል። አባ ኤዎስጣቴዎስ ከዚህ ሁሉ መንፈሳዊ ሕይወት በኋላ መስከረም 18 ቀን በ80 ዓመት ዕድሜው ከዚህ ዓለም በሥጋ ሞት ተለይቷል።

እሱ ከሞተ ከአንድ ዓመት በኋላ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ከአንድ አርመናዊ መነኩሴ ጋር ወደ አገራቸው ተመልሰዋል። ደቀ መዛሙርቱም በአባ አብሳዲ ዙሪያ ተሰብስበው በቀሃይን ደብረ ማርያም ገዳምን መሠረቱ። ሌላኛው ደቀ መዝሙር አባ ገብረ ኢየሱስ ወደ እንፍራንዝ ሔደው የራሳቸውን ገዳም መሠረቱ። ሁለቱ ወደ ሰሜን ሔደዋል።

የአቡነ ኤፌስጣቴዎስን ተረፈ አፅም በ1672 ዓ.ም ሆሳነስ ወይም ዮሐንስ የተባሉ አርመናዊ ጳጳስ ይዘው መጥተዋል። በቀዳማዊ ዮሐንስ /አእላፍ ሰገድ/ ትእዛዝ መሠረት የአቡነ አፅም ዐጤ ፋሲል /ስመ መንግሥታቸው ዓለም ሰገድ ነው።/ በጎንደር መዝረ መንግሥት መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በክብር እንዲያርፍ ሆኗል።

ምንጭ

- የቤተ ክርስቲያን መረጃዎች። ዝኒ ከማሁ ገጽ 622 - 624
- የቅዱሳን ታሪክ። ዝኒ ከማሁ ገጽ 95፣96
- ዳንኤል ክብረት። ከጣራ እስከ ጉዛራ። አዲስ ጉዳይ። ቅጽ 7 ቁ. 140 ጎንደር 2005። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት። ገጽ 30
- ዳንኤል ክብረት። ከጣራ እስከ ጉዛራ። አዲስ ጉዳይ። ቅጽ 7 ቁ.141 ጎንደር 2005። አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት። ገጽ 24፣25
- እርቅይሁን በላይነህ። ‹‹ቅድስት ጣራ ገዳም›› የቴሌቪዢን መርሐ ግብር ጽሑፍ